# የበሩ መክፈቻ

እዚህ በተበርናክሉ መገኘቴ መታደል ነው! ለእኔም፡ ትንሽ ያልጠበቅኩት ነበር። ዛሬ ማታ የጌታ እራት ምሽት ስለሆነ፣ በምችለው ጊዜ ሁሉ፡ በጌታ እራት ወቅት፡ መቀላቀል እወዳለሁ። ምክንያቱም... ሁሉም ክርስቲያኖች ጌታ እራት ለመቀበል በጉጉት ሊጠባበቁ እንደሚገባ አምናለሁ፡ ምክንያቱም ኢየሱስ፡ “ካልበላችሁ፡ ከእኔ ጋር ዕድል የላችሁም” ብሏል። ስለዚህ፣ በተበርናክሉ መ—መገኘት ሁል ጊዜ ልዩ መታደል ነ... ነው። ስለዚህ፡ ዛሬ ማታ፡ ወንድም ኔቪል ጉሮሮዬ ትንሽ ተዘግቷል ብሎኛል፡ እ—እና ለጉባኤውን መናገር እችል እንደሆነ ጠየቀኝ። ይህን በማድረጌ ደስተኛ እንደምሆን ነገርኩት። እንዲህ ከሆነም ማስታወቂያ መናገር እፈልጋለሁ...

2 ነገ ምሽት ወንድሞች ስብሰባ ያደርጋሉ፡ ነገ ምሽት የዚህች ቤተ ክርስቲያን፡ ባለአደራዎች፡ እና ነጋዴዎች ጋር፡ በመደበኛው የሰኞ ምሽት ስብሰባቸው የሚደረግ ሲሆን... ከኮንትራክተሩ ጋር በጋራ ለመወሰን ውሳኔ ያስተላልፋሉ። ማ—ማ—ማመልከቻዎቻችን እንደፀደቁ ሁላችሁም ተረድታችሁታል ብዬ እገምታለሁ፡ እናም ቤተክርስቲያንን መገንባት እንችላለን። ስለዚህ ይህ ጸድቋል፣ ስለዚህ ስራው በዚህ ሳምንት ሊጀምር ይችላል። እኔ እስከማውቀው ድረስ፡ ቤተክርስቲያን በዚህ ሳምንት ጀምራለች። እዚህ ጄፈርሰንቪል ውስጥ፡ ጥያቄያችን ተቀባይነት አላገኘም። እኛ ግን ወደ ኢንዲያናፖሊስ፣ ወደ ስቴት ደረጃ ወስድነው፣ እነሱም ፈቃድ ሰጡን፣ ስለዚህ እንገነባዋለን። ስለዚህ፡ በዚህ ሳምንት፡ ሥራ ሊጀመር ይችላል። ከነገ ምሽት ስብሰባ በኋላ ይታወቃል። ስለዚህ ነገ ምሽት ስብሰባው ካለቀ በኋላ፡ በዚህ ሳምንት ካልጀመሩ፣ የሆነ ነገር ከተፈጠረ፡ እና ኮንትራክተሩ በዚህ ሳምንት መጀመር ካልቻለ፡ በሚቀጥለው ሳምንት ይጀምራሉ።

3 በሚቀጥለው የሳምንቱ ቀናት፣ ቅዳሜ ምሽት፣ እሁድ ጥዋት እና እሁድ ምሽት፣ በሚቀጥለው ሳምንት፣ ቅዳሜ እና በሚቀጥለው እሁድ፣ ጌታ ቢፈቅድ፣ ከጥቂት ሳምንታት በፊት እንዳደረግነው፡ በድጋሚ ሶ—ሶ—ሶስት ስብሰባዎችን፡ ማድረግ እፈልጋለሁ። ከዚያ በኋላ... ይህ የሚሆነው ቅዳሜ ምሽት፣ ከዚያም እሁድ ጥዋት፣ እና እሁድ ምሽት ነው። ይህም፡ በዚህ ቀጣይ ወር አሥራ ሦስተኛውና አሥራ አራተኛው ይሆናል።

4 ከዚያ በኋላም እኔና አንዳንድ ወንድሞች፡ ወደ ኮሎራዶ እንሄዳለን፡ ለማደን ጉዞ እናደርጋለን፡ ከዚያም እንመለሳለን። የጌታ ፈቃድ ሆኖ፡ ተበርናክሉ፡ ቢጠናቀቅ፡ ምናልባት፡ ወደ ስብሰባዎች ከመመለሴ በፊት፡ አንድ ሳምንት ሙሉ፡ በራዕይ **በሰባቱ ማህተሞች** ላይ ጊዜ ማሳለፍ እወዳለሁ። ልክ በፊት... **ሰባቱን የቤተክርስቲያን ዘመናት** እንዳደረግነው፣ **ሰባቱ ማኅተሞች** ከዚያ በኋላ ይከተላሉ።

5 እና ምናልባት በሚቀጥሉት ሁለት ወይም ሦስት ሳምንታት ውስጥ፡ እኔ እንደማስበው እንደ ትንበያቸው፡ ለዚህ የሚመድቡትን የስራተኞች ብዛት ሲመለከቱ፡ ተበርናክሉን ሠርተን በአሥር፡ ወይም በአሥራ አምስት ቀናት

ውስጥ እንጨርሳለን፡ መጨረስ ይችላሉ፡ እንደዚያ ይመስለኛል። ስለዚህ አሁን ልናስተናግዳቸው ከምንችላቸው ሰዎች ቁጥር በእጥፍ፡ ወይም ምናልባት በሦስት እጥፍ፡ የሚበዙ ሰዎችን ለማስተናገድ እዚህ መቀመጫ ይኖረናል። ለዚህም ነው እስከዚያ ድረስ መጠበቅ ያለብኝ።

6 ምክንያቱም ባለፈው ጊዜ፣ ቅዳሜ እና እሁድ፣ በጣም አስፈሪ ነበር፣ ታውቃላችሁ። ቤተ ክርስቲያኒቱ በሯን ከመክፈቷ በፊት፡ ሰዎች በመገናኛው ድንኳን ውስጥ መቀመጫ ለማግኘት፡ ከቀትር በኋላ ሁለት ሰዓት ላይ ነበሩ። በማግስቱ ጧት፡ በአምስት ሰአት፡ ከአጠገቤ የምትኖር ነርስ፡ እንዲት ነርስ ከዚያ መጣችና፡ ስትናገር፡ “ከሌሊቱ አምስት ሰአት ላይ በተበርናክሉ ዙሪያ ብዙ ሰዎች ነበሩ” አለች። ስለዚህ፡ እንግዲህ ሰዎች፡ ገብተው፡ ቦታ ከሌለ፡ ተስፋ ቆርጠው ይሄዳሉ። እ—እና እንዲሁም የቆሙት ሰዎችም፡ ተጨናንቀው በየጥጉ ተጨናንቀዋል፡ አለ የተባለውን፡ በሙሉ ሞልተውታል። ሴቶች እዚያ ቆመው ሲያልባቸው፡ አይቻለሁ፣ ታውቃላችሁ፡ እና ላባቸው፡ እንዲህ ይንጠባጠባል። አንድ ሰው ወንበሩን፡ ለሌላ ሴት ለመስጠት ይነሣል፡ ከዚያም እግሮቹ እስኪጎዱ ድረስ ይቆማል፡ ለእሱም ሌላ ሰው ይለቅለታል። ታውቃላችሁ፡ ልክ እንደዚያ ነውና፡ ይህ የሚያሳዝን ነው፡ እና የታመሙ ትናንሽ ልጆች እና ሁሉም ነገር ያላቸው እናቶች አሉ፡ በጣም አስከፊ ነው።

7 ስለዚህ፡ አሁን ትልቅ ድንኳን በመገንባት ይህንን ለማጥፋት እየሞከርን ነው። እና ለልጆች ጥሩ ቦታ ይኖረናል... አንዳንድ ጊዜ፡ ስለሚያለቅሱ፡ ያቋርጡብናል፡ ስለዚህ፡ እናቶች ወደዚያ ሲሄዱ፡ አሁንም አገልግሎቱን እያዩ፡ እና በዚያ ክፍል ውስጥ፡ ስርጭቱን ለማዳመጥ እንዲችሉ ለዛ የሚሆን ክፍል ይኖረናል። ለሰንበት ትምህርት ቤቶች ክፍሎች ይኖሩናል እና ሁሉም ነገር እንደ ሁኔታው ይዘጋጃል። ይህም፡ ጌታ ቢፈቅድ፡ በሚቀጥለው ሳምንት፡ ይጀምራል።

8 ሁላችሁም መቶ ፐርሰንት በአንድ ድምጽ መርጣችኋል፣ ስለዚያም መብት ይኖረናል፡ አያችሁ። ቤተ ክርስቲያን ሉዓላዊት ናት። ቤተ ክርስቲያን የምትናገረው ነገር፡ ይሆናል። ባለአደራዎች ሆኑ ሌሎች... ባለአደራዎች፡ እያንዳንዳቸው፡ አንድ ድምፅ ብቻ አላቸው። ፓስተሩ አንድ ድምጽ ብቻ ነው ያለው። ቤተ ክርስቲያን ናት፣ የ—የቤተ ክርስቲያን ዲሞክራሲ፣ የቤተ ክርስቲያን ሉዓላዊነት ነው። ቤተ ክርስቲያን፡ በአጠቃላይ፡ ይናገራል። ይኼው ነው። ይህም እኛ ደግሞ እንወዳለን፡ እንደውም ጳጳስ ተዋረድ የበላይ ተመልካች ወይም የሚያዝን **ይህን ፡ ያንን፡** ወይም **ሌላውን** ምንም የለንም። በቤተክርስቲያን ውስጥ የሚናገረው፡ መንፈስ ቅዱስ ነው። ይህን ደንብ እወደዋለሁ፡ በጣም ጥሩ ነው።

9 እንዲህ ብዬ ጠየኳቸው፡ “ተበርናክሉን አፍርሰን ትልቅ ቤተ ክርስቲያን ለመገንባት የሚያስችል በቂ ገንዘብ እስክናገኝ ድረስ ሁላችሁ መጠበቅ ትፈልጋላችሁን? ” ጉዳዩን በባለአደራዎች ቦርድ አነጋግሬዋለሁ፣ እና ባለአደራዎቹ ጉዳዩን መፍታት አልቻሉም። ከዚያም እንደ ዋና የበላይ ተመልካች፡ መጥቼ ቤተ ክርስቲያኒቱን እንድጠይቅ፡ እኔን ጠየቁኝ። እናም፡ “ቤተክርስቲያኑን ለማስፋት እና ከነበረን በተለየ መልኩ ለማቅረብ፡ ሌላውን ሁሉ ለማድረግ፡ አሁን በቂ ገንዘብ አለን” አልኳቸው። እና፡ “አሁን ወዲያውኑ

ማድረግ እንችላለን፣ ካልሆነ ሌላ ቦታ ላይ፡ አዲስ፡ ቤተ ክርስቲያን ለመገንባት በቂ እስክንሆን ድረስ ገንዘባችንን እንቆጥበዋለን።"

10 በዚህ ጉዳይ ላይ ቤተክርስቲያኑ ድምጽ እንድትሰጥ፡ በአንድ ድምፅም "ቤተክርስቲያኑ ወዲያውኑ እንዲገነባ፣ ቤተክርስቲያኑ እንዲሰፋ" ተወስኗል። በዚያም በጸና አጽድቀነዋል።

11 የጄፈርሰንቪል ከተማ ምክር ቤት ጥያቄያችንን ውድቅ አድርገውብናል፣ ማድረግ እንደማንችል አሳወቁን። እናም ወደ ፊት ቀጠልን፣ ጥያቄያችንን በኢንዲያናፖሊስ ለስቴቱ አቀረብን። ወዲያውኑም፡ "ቀጥሉ፡" በማለት ቃላቸውን ሰጡን፡ ስለዚህ እሱን ለመገንባት መብት አለን። ስለዚህ ከተማዋ አሁን ምንም የሚያገናኘው ነገር የለም፡ የመንግስት ሃላፊነት ነው። ስለዚህ ፈቃድ አግኝተናል፡ አሁን ፈቃዱ በኮንትራክተሩ እጅ ገ—ገብቷል፣ እና በማንኛውም ጊዜ ለመጀመር ዝግጁ የሆኑ ይመስለኛል።

12 ኮ—ኮንትራክተሩ በነገው ምሽት፡ በሚቀጥለው ሳምንት መጀመር እፈልጋለሁ ካለ፡ እስከ **ሰባቱ ማህተሞች** ቀጣይ ስብሰባችን ድረስ... ስብሰባዎቹን እሰርዛለሁ። ነገር ግን ኮንትራክተሩ በሚቀጥለው ሳምንት መጀመር ካልቻለ፣ በሚቀጥለው እሁድ፣ በሚቀጥለው ቅዳሜ እና እሁድ፣ ከመሄዱ በፊት እነዚህን ስብሰባዎች አደርጋለሁ።

13 እናም በዚህ እሁድ ላደርገው አስቤ ነበር፣ ነገር ግን ዛሬ ምሽት የጌታ እራት ጊዜ እንደሆነ አስተዋልኩ፣ ስለዚህ በዚህ እሁድ ትቼዋለሁ። በእርግጥም፡ እንደዚህ ያለ ብዙ ሕዝብ ይዘን፡ የጌታ እራትን በቀላሉ መቀበል አትችሉም፡ ትልቅ ቤተ ክርስቲያን ሲኖረን ግን እንችላለን።

14 አሁን፡ ቀጣዩ ፕረዚደንት የሚሆነን ተሰጥቶናል። ኦ... ኦህ፡ ምን ማለት እንደፈለግኩ አውቃችኋል፣ ወደ ሂከርሰን ቤተሰብ በቅርብ ተቀላቅሏል። ፒያኖ ተጫዋች የሆነችው እህታችን፡ ወደ ፒያኖ መጥታ ኮርድ ብትሰጠን፡ ከቻልሽ "ብሪንግ ዘም ኢን፡" የሚለውን፡ ወይም እንደዚያ አይነት ሆኖ እነሰ ያለ መዝሙር ስጪን። በሂከርስን ቤተሰብ ዘንድ ለረጅም ጊዜ ሲጠበቅ የነበረው፡ ይህ ቆንጆዬ ሽበላ ልጅ፡ ደርሷል። እጅግ የሚያምር ህጻን ልጅ፡ በርግጥም ለሂከርሰኖች ጌጥ ነው። ለእኛም ሁሉም ጌጦቻችን ናቸው፡ እኛ እነወዳቸዋለን እነሱ በእውነት ወንድም እና እህታችን ናቸው። ቤተሰቡን ውደ ፍጹም መነቃቃት ያመጣው ይህ ትንሽ ልጅ፡ በቤተሰባቸው ውስጥ በመወለዱ እናመሰግናለን። እንግዲህ ከቻሉ፡ ህጻኑን ለእግዚአብሔር አደራ ለመስጠት አባት እና እናት ህጻኑን ይዘው ወደዚህ ይምጡ። አሁን፡ መጽሐፍ ቅዱስ ሲናገር፡ "እጁን ይጭንባቸው ዘንድ፡ ይባርካቸውም ዘንድ፡ ጨቅላዎችን ህጻናትን ወደ እርሱ አመጧቸው።"

15 በዚህ ጊዜ፡ በዓለም ላይ "የህጻናት ጥምቀት" በሚባል ነገር የሚያምኑ ሰዎች አሉ። ያም ማለት፡ እነዚህን ህጻናት ይወስዷቸዋል እንጂ፡ በጭራሽ አያጠምቋቸውም፡ ምክንያቱም፡ በውሃ ብቻ ይረጯቸዋልና። ነገር ግን፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፡ ህጻናት ይቅርና፡ ትልቅ ሰውም፡ የተረጨበት ቦታ አናገኝም።

16 እንግዲህ ጥምቀት የጸጋ ሥራ በውስጥ ማንነት መፈጸሙን የሚያሳይ ምስክር ነው። ሕፃናት ግን ስለ ኃጢአት ምንም ግንዛቤ የላቸውም። ለዚህም ነው፡ ኢየሱስ በመስቀል ላይ ሲሞት፡ የአለምን ኃጢአት ሊያስወግድ የሞተው። ጨቅላው ልጅ ሰው ሲሆን፡ ወደዚህ ዓለም ሲወለድ፡ በግል ኃጢአት የሌለበት ነው፡ ስለዚህም ንስሐ ሊገባ የሚገባው ምንም የለውም። ነገር ግን፡ ያ ሲሆን ግን፡ ይህንን ኃጢአት የሚያስወግደው የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ነው። እርግጥ ነው፣ ሕፃኑ በኃጢአት ተወልዷል፣ በዓመጽም ተጸንሰዋል፣ ወደ ዓለም የመጣው ውሸትን እየተናገረ፣ በባሕርዩ ኃጢአተኛ ነው፣ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ግን ለዚያም ያስተሰርያል። ህፃኑ ልጅ የተጠያቂነት እድሜ ላይ ሲደርስ፡ መልካሙን ከክፉ መለየት ሲያውቅ ግን፡ ከዚያም በሠራው ነገር ንስሃ መግባት አለበት። አሁን ኃጢአቱ በኃጢአት እንደተወለደ ኃጢአት ብቻ ነው፣ የሰው ኃጢአት ነው፣ ይህ ኃጢአት አዳምና ሔዋን የሠሩት ኃጢአት ነው፥ ያም በእግዚአብሔር፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ተደምሰሷል። ሕፃኑ ንስሐ የሚገባበት ኃጢአት የለበትም፡ አንድ ጊዜ ኃጢአት ከሠራ በኋላ ግን ንስሐ መግባት አለበት። አያችሁ? ንስሐ ከገባም በኋላ፡ ለመጠመቅ ጊዜው አሁን ነው፡ በዚያም በጥምቀት ተጠመቀ።

17 እስከዚያው ጊዜ ድረስ፡ የመጽሐፍ ቅዱስ መመሪያዎች እንከተላለን፡ እንዲህ የሚለውን፡ "እጁንም ይጭንባቸውና፡ ይባርካቸው ዘንድ ሕፃናትን ወደ ኢየሱስ አመጡ።" ዛሬ ማታ እነዚህ ድንቅ ወላጆች ይህንን ሕፃን ወደ ፓስተር እና ወደ እኔ፡ ለጌታ እንዲሰጥ አምጥተውታል። በክርስቶስ ተወካዮች እጅ ውስጥ በማስገባት፡ በክርስቶስ እጅ ውስጥ እንዳስቀመጡት ይሰማቸዋል። ስለዚህ፡ በእምነት፡ ሕፃኑን ወደ እግዚአብሔር እናቀርባለን፡ እርሱን እዚህ ስላደረሰው ምስጋና ለማቅረብ፡ እና እግዚአብሔርን እንዲባርከው እንጠይቃለን፡ "ህጻናትን ለጌታ መስጠት" የምንለው ይህ ነው።

18 እንግዲህ፡ ስለ ገዛ ልጆቼ ምን እንደማስብ ታውቃላችሁ። ዛሬ በክብር ያረፈች አንዲት ትንሽ ልጅ አለችኝ፣ እሷም እዚህ በመሠዊያው ላይ፡ ለጌታ ተሰጥታለች። ዛሬ ማታ፡ ከኋላ ከተቀመጡት መካከል አንድ ወንድ እና አንዲት ሴት ልጆቼ አሉ፡ ከዚህ በፊት አልተጠመቁም። እንደኛዋ፡ አስራ አንድ ዓመቷ ናት፡ ሳራ ነች፣ ዛሬ ስለ ጥምቀት፡ እያወራኋት ነበር። ዮሴፍ ገና የሰባት ዓመት ልጅ ነው፣ ስለዚህ ገና በጣም ትንሽ ነው፣ እስኪፈልግ ድረስ... ካልተመኘው በቀር፡ እግዚአብሔር በልቡ ላይ ካኖረ፡ ያኔ አደርገዋለሁ። ነገር ግን፡ ትንንሽ ልጆች፣ ለጌታ ብቻ እሰጣቸዋለሁ፣ ምክንያቱም ቅዱሳት መጻሕፍት የሚያስተምሩት ይህ ነው።

19 ወንድም ኔቪል፣ ወደዚህ ቆንጆ ልጅ አሁን ከእኔ ጋር ብትመጣልኝ። ፈርቼ ነበረ... ሆሊን ነው አይደል? ሆሊን? አዎን፡ ሆሊን፡ ጁኒዬር። ስቴፈን ሆሊን። እሺ፡ በጣም ጥሩ። ኦህ፡ የተኛ መስሎኝ ነበር። ምንም ቢፈጠር፡ ይህ የሂከርሰን ባህርይ ነው። በቀደም ሳየው፡ "ፕረዚዳንቱ" አልኩት፡ ሌላም ብዬዋለሁ። እና፣ በእርግጥ፣ ስለ እሱ እንደ "ፕሬዚዳንት" ማውራት፡ ለእሱ በጣም ሲያንሰው ነው፡ አያችሁ። እንደምን አለሽ? መቼም፡ ለእያንዳንዷ እምላካዊት እናት ውድ ሀብቷ መሆን እንዳለበት አውቃለሁ። አይመስላችሁም? በጣም ቆንጆ ነው። አሁንም፡ ወንድም ሂከርሰን እና እህት ሂከርሰን ሆይ፣ እኔ እንደ ክርስቶስ

አገልጋይ፣ እንደ ፓስተራችሁ፣ ይህንን ህፃን፣ በእምነት፣ በኢየሱስ ክርስቶስ እቅፍ ውስጥ፣ በምትፈልጉት እቅፍ ውስጥ አስገብቼዋለሁ።

20 እኔ እና ፓስተር እጆቻችን በህጻኑ ላይ ጭነን እንደቆምን ሁላችንም አንገታችንን ዝቅ እናደርጋለን።

21 የሰማይ አባታችን፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ህጻናትን ወደ አንተ አመጡ፡ ይህም አንተ እጆችህን ትጭንባቸው ዘንድ እና ትባርካቸው ዘንድ ነው። በእውነትም፡ ጌታ ሆይ፡ ባርከሃቸዋል። አሁንም አንተ ያደረግሃቸውን ነገሮች፡ ምሳሌህን ለመከተል፡ መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ እና አንተ እንደ አደራረግህ ተምሣሌት በመከተል፡ ጌታ ሆይ፡ ተጠንቅቀን አድርገናል። እና እኚህ አባት እና እናት፣ ወንድም እና እህት ሂከርሰን፣ በዚህ ተበርናክል ተወዳጅ ደቀ መዛሙርቶቻችን፡ አደራ የሰጠሃቸውን ይህን ትንሽ ደስታ ወደ እኛ አምጥተውታል። ጌታ ሆይ፡ ከአንተ የመጣ ነው። ይህን ልጅ ሰጥተሃቸዋል። አሁንም ትንሿን ህይወቱን ለአንተ ለመስጠት፣ ለአንተ አገልግሎት ለመሆን ይፈልጋሉ። ይህንን ልጅ እንድትባርከው፡ ረጅም እድሜም እንድትሰጠው እጸልያለሁ። ከተቻለ፡ የጌታን መምጣት ለማየት በሕይወት ይኑር። በሚገኝበት ቦታ ሁሉ እንድትባርከው እጸልያለሁ። በዚያ ሆኖ እንደተወለደ፡ በክርስቲያን ቤት ይደግ። እና በዚህ ቤት ውስጥ ይቀጥል። ቢቻልም፡ አባት እና እናት ሕፃኑን በቸቢት ላይ ሆኖ፡ ወንጌሉን ሲሰብክ ለማየት ያብቃቸው። አባት ሆይ፡ ባርያዎችህ ናቸውና፡ በኋይት ሀውስ ዙ—ዙፋን ላይ፡ ወይም በሌላ ተቀምጦ ከሚያዩት ይልቅ፡ በዚያ መልኩ ቢያዩት ይመርጣሉ፡ ለእግዚአብሔር ሥራ መስጠት እና በረከት እንዲሆን ይፈልጋሉ።

22 አሁን አባት ሆይ፡ ልጁን እንድትባርክ፡ እጸልያለሁ። የእግዚአብሔር ፀጋ በእርሱ ላይ ይሁን፡ በህይወት ዘመኑ በሙሉ ጤናማ እና ደስተኛ ይሁን። አባት እና እናት ሲያድግ ለማየት በህይወት ይኑሩ፡ ደግመን እንጠይቃለን። በሰምህ የምንባርከው ይባርክ።

23 አሁንም፡ ህጻን ስቴፈን ሆሊን ሂከርሰን ሆይ፡ እነሆ ለኢየሱስ ክርስቶስ አደራ ሰጥቼሃለሁ፡ ይህም የጠየቅናቸው በረከቶች በአንተ ላይ ይደርሱ ዘንድ ነው። ታናሽ ወንድሜ ሆይ፡ ጤናማ እና ጠንካራ ሁን፡ ለእግዚአብሔርን ክብር ኑር። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እንጠይቃለን። ኣሜን።

እግዚአብሄር ይባርክህ። እግዚአብሔር ሁላችሁንም ይባርካችሁ። በጣም መልካም ልጅ።

> መቼም የማናረጅባት፣ መቼም በማናረጅባት፣
> በማናረጅባት በዚያች ምድር፥
> መቼም የማናረጅባት፣ መቼም የማናረጅባት፣
> በማናረጅባት በዚያች ምድር።

24 ድንቅ ይሆናል አይደል? ወጣቶቹ አዋቂዎች ይሆናሉ፡ አሮጌው ወጣት ይሆናል። ይደንቃል፡ አይደል? መቼም አንታመምም፣ አናዝንም፣ አንሞትምም።

25 አሁን፣ ወንድም ኔቪል፡ ስብሰባዎችን አስታውቋል። አሁንም በድጋሚ፡ ደግሜ፡ ይህን ስብሰባ፡ እና እሱ የተናገራቸውን ስብሰባዎች አትርሱ፡ ማለት እፈልጋለሁ። እንዲሁም፣ ከብዙ አመታት በፊት ጀምራ ወደዚህ ቤተ ክርስቲያን

ትመጣ የነበረችው ወይዘሮ ፎርድ፣ ከጥቂት ቀናት በፊት፣ ወደ ልጇ ቤት ወሰድኳት፣ የሰማንያ ዓመቷ ነበረች፣ ጌታን ለማግኘት ትናንት ማታ በሰምንት ሰዓት ሄደች፣ ይመስለኛል። እኔና ፓስተር የቀብር ሰነ ሰርዓቷን፡ በኮትስ በሚገኘው ቻፕል ውስጥ እናስፈጽማለን እሮብ፡ በሚቀጥለው ረቡዕ ከ—ከአስር እስከ አስር-ተኩል ላይ፡ እናደርጋለን። ወይዘሮ ፎርድ፣ ወይዘሮ... ሰሙ ማን ነበር ረሳሁ መሰለኝ... የሌዊ፣ ወይዘሮ ሌዊ ፎርድ። የኛ... በመጽሐፌ ውስጥ የማወራው የሎይድ ፎርድ እናት እ—እሷ ናት፣ ያንን የቦይ ሰካውት ልብስ እንደሚሰጠኝ ነግሮኝ፡ በኋላ ግን አንድ እግር ብቻ ያሰቀራት እሱ ነው። እና፡ የ—የእሱ ልጅ እናቱ ናቸው። እናም ምሰኪኗን አሮጊት፡ በቀደም ወደዚያ ወሰጄ ጸለይኩላት። ከጌታ ኢየሱስ ጋር ለመሆን ሄዳለች።

26 እንግዲህ፣ ጌታ ቢፈቅድ፣ ማሳወቅ ያለብኝ ነገር አለ አገልግሎቶቹን፡ በሚቀጥለው ሳምንት እዚህ የሚሆኑ ከሆነ፣ በቀጣይ ሳምንት በሚኖረን አገልግሎት፡ እኔ እንደሚመስለኝ ከሆነ፡ በ—በ—በመጪው ሳምንት ለመናገር ያቀድኳቸው ነገሮች፡ እዚህ ጽፌ ይዣቸዋለሁ። ይ—ይመስለኛል... በዚህ መጽሐፍ ውስጥ እንዳስቀመጥኩት እሰባለሁ፡ እድርጌ እንደሆነም እንዳለሆነም እንጃ። አዎን፡ አገኘሁት። ጌታ ቢፈቅድ፣ ቅዳሜ ምሽት **አንድ ሰው ለምን በሌላ ሰው ሕይወት ላይ ተጽዕኖ እንደሚያሳድር** በሚለው ርዕሰ ላይ መሰበክ እፈልጋለሁ። እና እሁድ ጠዋት ደግሞ **የፒራምድ ራሰ መክደን** በሚል ርዕሰ እሰብካለሁ። እሁድ ማታ ደግሞ **መሪዬ**፡ በሚል ርዕሰ ይሆናል፡ መጪው እሁድ ማታ፡ **መሪዬ**። አሁን እኔ እንደወጣሁ፡ ትንንሽ ሐሳቦችን ለመሰብሰብ እንደታርኩኝ፡ ጌታ እነዚያን ነገሮች ይባርክ እና ይርዳኝ።

27 አሁን፣ ዛሬ ማታ ቶሎ ብለን ጥቂት ነገሮችን ለማየት እንፈልጋለን። በነገራችን ላይ፡ ቢሊ ቀደም ሲል ያመጣቸው—ደብዳቤዎች፡ አሁን የመጣ ፖሰታ ተቀብያለሁ፡ በሚቺጋን ጥቂት ወንድሞች አሉ፡ እና ይህ የመጣው ብዙ ጣጣ ካለው ከአገልጋዮች ማህበር ነው። ነገሮችን የሚያበላሹት በዚያ ነው፡ አያችሁ። እንዲያውም፡ እኔ ወደዚያ እንደላክኳቸው የሚናገሩ አንዳንድ ወንድሞች እንዳሉ ይናገራል፣ እንዲሁም ወንዶች ሚሰቶቻቸውን ትተው መንፈሳዊ የትዳር አጋራቸውን እንዲያድኑ እየሰበኩ እንደሆነ፡ እና በፍጹም የ—የማልሳሳት መሆኔን ይናገራሉ። እንዲህ ብሎ የለም... እና፡ አቤት፡ እነዚህ እሰካሁን ከሰማችኋቸው እጅግ አሰፈሪ ነገሮች ናቸው። የአገልጋዮች ማኅበርም ይሄን ይዘው፡ ሰለዚህ ጉዳይ ደብዳቤ እየጻፉልኝ ይገኛሉ፡ እኔ እነዚህን ወደዚያ እንደላክኩ እና ብዙ ግራ መጋባት እንደፈጠረ ነው። አንዳንዶቹ ትንቢት ይናገሩና አንዱ **ይቺን** ሴት ትቶ **ያቺን** ያግባ ይላሉ። አሁን፣ ይህች ቤተ ክርሰቲያን እንዲህ ዓይነት ከንቱ ነገርን እንደማንደግፍ ታውቃለች።

28 በመጽሐፍ ቅዱሰ እናምናለን። እኛ እናምናለን አንድ ወንድ ሴት ሲያገባ፡ ሚሰቱ ናት፡ እና ሞት ብቻ ይለያቸዋል። ይኼው ነው። በዚ ዓይነት ነገር አናምንም። በነጻ ፍቅርም፡ አናምንም። በእነዚህ ነገሮች አናምንም። መጽሐፍ ቅዱሰ ብቻ፡ እና ብቻውን በሙላት እናምናለን። ሰለዚህ ኮፒ ላርገው፣ ይህን ደብዳቤ ቅጂ አዘጋጅቼ፡ መልሰ ሰጥቼ በመጽሔቶች ላይ አወጣለሁ፡ ይህ ደግሞ ጉዳዩን እልባት ይ—ይሰጠዋል። በማንኛውም ሁኔታ፡ ይህ መልሰ እንደሚሰጣቸው፡ ተሰፋ አደርጋለሁ።

29 እስኪ ዛሬ ማታ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ከመክፈታችን በፊት፣ ጌታችን እናነጋግረው።

30 የሰማይ አባታችን ሆይ፣ በጌታ በኢየሱስ ስም፡ ወደ ምህረትህ ዙፋን እንቀርባለን፡ የእግዚአብሔርን የክብር ባለጠግነትን ሊገልጥልን ከክብር የወረደው ታላቅ እርሱ ነው። የእግዚአብሔር መገለጥ ስለ ሆነው ለእኛም በግል ስለተገለጠልን፡ ስለዚህ ታላቁ ኢየሱስ እጅግ እናመሰግንሃለን። በእርሱም ከኃጢአታችን ቤዛ አገኘን። አሁንም በእርሱ አምነናልና፡ ከሞት ወደ ሕይወት ተሻግረናል። ስለ እርሱ፡ እንዲህ ተብሎ ተጽፎአልና፡ "ቃሌን የሚሰማ፡ የላከኝንም የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው፥ ከሞት ወደ ሕይወት ተሻገረ እንጂ፡ ወደ ፍርድ አይመጣም።"

31 ዛሬ ማታ፡ ጌታ ሆይ፡ ቃልህን ባርክ። እና በአጭር ጊዜ ውስጥ የጌታ እራትን ለመውሰድ እዚህ ተገኝተናል። ክርስቲያን፣ የመንግሥቱ ዜጎች በመሠዊያው ዙሪያ ይሰበሰባሉና፣ በእዚያም "የጌታ እራት" ብለን ከምንጠራውን ይቀበላሉ፡ ይ—ይህም አንተ ከተውክልን ቁርባን—ትንሽ ቁራሽ ነው፡ ይህም ለኃጢአታችን እንደ ሞትህ፡ በሦስተኛውም ቀን እንደ ተነሣህ፡ እና ለዘላለም ሕያው እንደሆንህ ማመናችን ለማሳየት ነው፡ በታዘዝነው መሰረት ቅዱሳት መጻሕፍት እንደሚሉት፡ ይህ አንተ እስክትመለስ ድረስ እናደርገዋለን። ልባችንን ከመጥፎ ሀሳቦች እና ከታላቁ ፈቃድህ ተቃራኒ የሆነውን ካደረግነው ሁሉ ቀድሰን። አባት ሆይ፡ ይቅር በለን፡ ዛሬ ማታም ከጸጋህ ስጠን። አሁን ከቃሉ ውስጥ ስናነብ፡ እና ስለ እሱ ስንናገር፡ የሕይወትን እንጀራ ቁረስልን። በጌታ በኢየሱስ ስም፡ እንጠይቃለን። ኣሜን።

32 እንግዲህ በራዕይ መጽሐፍ፡ ከ 20ኛው ምዕራፍ፡ አንድ ቁጥር ብቻ ላነብ እወዳለሁ፡ ማለቴ የ 20ኛው ምዕራፍ 1ኛው ቁጥር።

**የጥልቁ መክፈቻና ታላቁን ሰንሰለት በእጁ የያዘ መልአክ፡ ከሰማይ ሲወርድ አየሁ።**

33 አሁን ከዚህ በመነሣት፡ ከዚህ ጽሑፍ አውድ በመነሳት፡ መሆን ካለበት፡ ወይም ከዚህ ተነሰቼ ርዕስ ብሰጠው፡ ለሚቀጥሉት ሃያ ወይም ሃያ-አምስት ደቂቃዎች፣ **የበሩ መክፈቻ**፡ ብዬ ልጠራው እፈልጋለሁ። አሁን፡ "መክፈቻዎች" ብዬ መ—መጥራት አልፈለግሁም፡ ምክንያቱም "የመንግስቱ መክፈቻዎች" ለጴርጥሮስ ተሰጥቶታል። ይህንን ግን **የበሩ መክፈቻ**፥ በማለት መሰየም ወደድሁ። እና ወዲያውኑ ከዚህ በኋላ፡ ዛሬ ማታ ከመውሰዳችን በፊት፡ ስለ ጌታ እራት ጥቂት አስተያየቶችን መስጠት እፈልጋለሁ።

34 አሁን፡ መክፈቻ። አሁን እዚህ ጋር በእጁ መክፈቻ ይዞ፡ ከሰማይ ስለመጣው መልአክ ሰናነበው፡ አንድ ነገር አስተዋልሁ። ራዕይ 13 ወይም 19 ላይ ይመስለኛል፡ ሌላ መልአክ መክፈቻ ይዞ፡ እናየዋለን። እና መክፈቻ፡ የመክፈቻ ዋናው አላማ፡ የተቆለፈ ነገርን፡ ወይም የሆነ ነገር መክፈት ነው፡ ወይም መቆለፍ ያለበትን ነገር። መክፈቻ የሚሰጠን ለዚያ ዓላማ ነው።

35 አሁን፣ ብዙ አይነት መክፈቻዎች አሉ፣ ምክንያቱም ብዙ የመክፈቻ አጠቃቀሞች አሉን። የመጋዘኖች መክፈቻዎች አሉ። የቤታችሁ መክፈቻ አለ፡ የመኪና ቁልፍ አለ። ሁሉንም መክፈቻ እንላቸዋለን፡ እንዲሁም መክፈቻዎች

ናቸው። ብዙ ጊዜ፡ ሊባዙም ይችላሉ። ወይም ደግሞ ለቤት ከሆነ፡ አንዳንዴ የምንሰራው ነገር አለ፡ ሰሙ ማን ነበር፡ የብረት መክፈቻ። በሌላ አገላለጽ፣ በእጀታ የተሰራ የቁልፍ አይነት፡ በውስጡ ይጫወታል፡ ያ—ያ መቆለፊያውን በተለየ መንገድ ይቆልፈዋል የትኛውንም አይነት በር ይከፍታል፡ “የብረት መክፈቻ” ይባላል። የበርካታ መክፈቻዎች የብረት ፍሬም ነው፣ በዚያ መንገድ ሊከፈት ይችላል፣ ቤቶቻችን ላይ ወይም የቤት መኪኖቻችን ላይም እንዲሁ፡ የሚባዛ ነው። ሌላው ደግሞ...

36 የትኛውም አይነት መክፈቻ በእጅህ ሰር ጥቅም ላይ ካልዋለ ድረስ የቱንም አይነት በር መክፈት አይችልም። መክፈቻውን የሚጠቀም አካል ሊኖር ያስፈላጋል። መክፈቻው እራሱን በራሱ መጠቀም አይችልም። መክፈቻውን የሚያንቀሳቅስ አካል ያስፈልጋል።

37 ልክ እኔ እየተጠቀምኩበት እንዳለው እ—እንደዚህ ማክራፎን ነው። ማይክራፎኑ ጸጥ ይላል። የሚጠቀምበት አካል እስከሌለ ድረስ፡ በራሱ አይናገርም። በእሱ በኩል የሚናገር ነገር ሊኖረው ይገባል። ስለዚህ፡ ከማይክሮፎኑ አይደለም፡ ከድምጹ ወይም—(ከጀርባው) ካለው ማይክሮፎኑ ከሚያስተላልፈው—የአየር ሞገድ፡ ወደ ጆሮአችሁ ይደርሳል።

38 አሁን፡ የወንጌል ሰብከትም ያው ነው። እኛ አገልጋዮች፡ እራሳችን፡ ወንጌል አይደለንም። ነገር ግን በእኛ በኩል የእግዚአብሄርን ድምጽ፡ በሰዎች፣ ወደ ሰሚ የምናስተላልፍ አስተላላፊዎች ብቻ ነን።

39 ራዕይ ተመሳሳይ ነው። በዚህ ጊዜ ሰለ ራእይ ለቤተክርስቲያን የምለው ምንም ነገር የለኝም። መንፈስ ቅዱስ ሲያሳየኝ ግን፡ በመጀመሪያ፡ ራእይ አያለሁ፡ ከዚያ በኋላ ወደሚመለከተው አካል አስተላልፈዋለሁ። ስለዚህ የእኔ አልነበረም፡ እኔ፡ ራእዩ እኔ አልነበርኩም፡ እኔ። ራእዩን የሰጠው እግዚአብሔር ነበር፣ እናም የራእዩን መልእክት ለህዝቡ ለማድረስ፡ እንደ አስተላላፊ ሆኜ አደረኩ።

40 አሁን፡ መክፈቻም ያው ነው። ይቅርታ አርጉልኝ። መክፈቻ በርን በሚከፍት እጅ የሚያዝ ነገር ብቻ ነው። እያችሁ፡ እጅ ይጠይቃል። አሁን፡ ዛሬ ማታ በዚህ መክፈቻ ዙርያ እናገራለሁ፡ ይህም ይህ መክፈቻ መያዝ የሚችል አንድ እጅ ብቻ ነው፡ ያም የእምነት እጅ ነው። ይሄኛውን መክፈቻ መያዝ የ—የሚችል ብቸኛው ነገር ይህ ነው። እና እጆች ሌሎች ቁልፎችን ይይዛሉ፡ ለዚያም የእምነት እጅ ያስፈልገዋል።

41 እንግዲህ፣ የእውቀት ቁልፍን እንደ ምሳሌ እንውሰድ። አሁን፣ አንድ ሰው፡ እውቀትን ለማከማቸት ከሞከረ፣ እያችሁ፣ እንግዲህ፡ የዚያም መክፈቻ አለ። ይህ ሰው መሆን የሚገባው የሆነ ነገር ይኖራል። እንዲህ መሆን አለበት... መፃህፍቱንና ትምህርቱን ለማግኘት፡ አንድ ነገር አይቻልም... .ማንም ሊማርለት አይችልም። ሊያስተምሩት ይችሉ ይሆናል፡ ግን መማር ግን የእሱ ፈንታ ነው። ይህንንም ለማሳካት ብቸኛው መንገድ፡ መክፈቻውን መያዝ አለበት፡ ይህም የሚገልጠውን ወይም የሚከፍተውን-... የሚፈልገውን እውቀት የሚገልጥለት ነው።

42 ለምሳሌ አንዳንዶች፡ ፒያኖ… ወይም ሙዚቃ መጫወት የሚፈልጉ ሰዎች አሉ። በእርግጥ እንዴት እንደሚያደርጉት አያውቁም፣ ግን ወደዚያ ሊሄዱ ይችላሉ መምህሩም በትምህርት ላይ ትምህርት ይሰጣቸዋል፡ በዚህም ፈጽመው ላይማሩት ይችላሉ። የዚያን መክፈቻ ምስጢር መያዝ አይችሉም፡ ሪትም እና የዝማሬ ድምጾች እና ሁሉም ነገር እንዴት እንደሚጣመሩ ሊረዱት አይችሉም። መክፈቻው ይጠይቃል።

43 ሒሳብ፣ ለሒሳብም መክፈቻ አለው፣ እና ያንን እንዴት መቆጣጠር እንዳለባችሁ ማወቅ አለባችሁ። አራት ረድፍ ቁጥሮች ወስደው፡ ጣቶቻቸውን፡ እያንዳንዳቸው ጣቶቻቸውን በአንድ ረድፍ ቁጥሮች ላይ አድርገው፡ ከዚያም ወደ አምስት ወይም ስድስት ረድፍ ቁጥሮች **እንደዚህ** ዝቅ ብለው፡ መልሱን መጨረሻ ላይ የሚያስቀምጡ ሰዎችን አይቻለሁ። ከየትኛውም ረድፍ ጀምሮ፡ ከአንድ እስከ ዘጠኝ ድረስ አራት ረድፎችን በአንድ ጊዜ ማስላት ይችላሉ። እንግዲህ፡ እኔ ጣቶቼን እና አውራ ጣቴን ካልተጠቀምኩ በቀር፡ አንድ ረድፍ ለማስላት እንኳ እቸገር ነበር፡ እ—አንዲት ረድፍ ብቻ ለማስላት። ያንን መክፈቻ በጭራሽ ማግኘት አልቻልኩም። ግን፣ እያችሁ፣ አንዳንድ ሰዎች ያንን ቁልፍ አላቸው፣ እንዴት እንደሚያደርጉት ያውቃሉ።

44 እና እውቀትን ለሚፈልግ ሰው፡ የእውቀት መክፈቻ አለ። ለሳይንሳዊ ምርምር፡ የሳይንስ መክፈቻ አለው። አሁን፡ ይህም፡ ትልቅ መክፈቻ ነው። ሰዎች ያንን መክፈቻ እየፈለጉ ይገኛሉ።

45 ለምሳሌ ከተወሰነ ጊዜ በፊት አተምን ደረሱበት፣ አቶሞች መኖራቸውን አወቁ፡ አተሞች ሞለኪውሎችን እና ሁሉንም ነገር ሊፈጥሩ ይችላሉ። አሁን፡ ምርምር ውስጥ ገቡና፡ አንድ ሰው እንዲህ አመነ ማለት አተም ሁሉንም በአንድነት የያዘ ስለሆነ፡ ይህ አተም በራሱ ላይ እንዲሽከረከር ቢችል፣ ከዚያ በውስጡ ያለውን ይከፍታል። ምክንያቱም፡ ሁሉም ነገር በአቶም አንድ ላይ እንደሚያያዝ፡ እናውቃለን። አሁን፡ ይህ ምሰሶ በአተሞች የተገነባ ነው። እናንተም በአተሞች የተያያዛችሁ ናችሁ። ሣሩ፣ ዛፎቹ፣ ሁሉም ነገር ከአቶሞች ጋር አንድ ላይ ተያይዟል። እሺ፣ ይህ አተም፡ ሁሉም በአንድ አቅጣጫ የሚሽከረከር፡ ድንገት ተከፍሎ ወደ ተቃራኒው አቅጣጫ ቢሽከረከር፡ ያ ጥፋት ያስከትላል። እና አሁን፡ ታላላቅ ሳይንቲስቶች ይህ ሊሆን እንደሚችል አመኑ፡ እናም ስራቸውን ሰሩ ከዚያም ሰሩ፡ ሰዓታት በሰዓታት፡ ሳምንታት በሳምንታት፡ ከዓመት ዓመት በማደራጀት፡ እስኪደርሱበት ድረስ ተጉ።

46 ስለ ብርሃን፡ ቶማስ ኤዲሰን፡ የነበረ፡ ይመስለኛል፡ ብርሃንን በተመለከተ ይህ ሰው ኤሌክትሪክን በመጠቀም ብርሃን ማመንጨት የሚያስችል እውቀት እንደነበረው ይናገራሉ። የኤሌክትሪክ አምፖሉን የፈጠረው እሱ ነው። ሲመሽ ለመተኛት እንኳን ፈቃደኛ አልነበረም። ሳንድዊች በእጁ ይዞ ምግብ እየበላ፡ እዚያ ተቀምጦ እያሰበ ይሰራ ነበር። በአእምሮው ውስጥ የሆነ ቦታ፡ አንድ ነገር ማድረግ ትችላለህ የሚለው ነገር ነበር። እሱ ምን ነበር? መንገዱን ሊከፍት የሚችል መክፈቻ ነው።

47 ከቅርብ አመታት በፊት፡ የቀልድ ድራማዎችን የመጻፍ ችሎታ እንዳለው የሚያስብ እ—አንድ ሰው ነበር። ይህን መክፈቻ በእጄ ይዣለሁ ብሎ አመነ። እናም ፈለገ… ሄደ… መኖሪያውም በካንሳስ አደረገ። በካንሳስ ከተማ

ወደሚገኘው አንጋፋው ጋዜጠኛ በመሄድ፡ አንዳንድ ጽሑፎቹን አመጣለት። አዘጋጁ እንዲህ አለው፡ “ወዳጄ፣ ገና አልደረስክበትም። አንተ፣ መሞከር አያስፈልግህም፣ አንተ——የዚህ ብቃት የለህም።” ይህ መልስ ግን አላረካውም። በውስጡ እንዳለ ያውቃል። ወደ ኋላ ይመለስና፣ ብዙ ሙከራዎችን ያደርጋል፣ እሱ ግን (አዘጋጁ) አይቀበለውም ነበር። በመጨረሻም፡ ወደ ሌሎች ቤቶች ሄደ፣ እነሱም እንዲሁ፡ “ወዳጄ፣ አንተ ገና አልደረስክበትም። አይሳካልህም፡” አሉት። እሱ ግን ማድረግ እንደሚችል ያምን ነበር። መንገዱም ያ ነው፡ በእጁ የሆነ ነገር አለ! በመጨረሻ፡ ለቤተ ክርስቲያን ኤዲቶሪያል፡ ወይም ለሆነ ነገር፣ ለቤተ ክርስቲያን ትንሽ የቀልድ ድርሰት ዓይነት፡ ትንንሽ ቁርጥራጮችን በመጻፍ ሥራ አገኘ። እናም አይጦች-የሚሽከረከሩባት ወይም በአይጥ-መንጋ የተወረረች ትንሽ ጋራጅ ተከራየ፡ አይጦች እዚያም እዚም፡ አንሶላው ላይ የሯሯጣሉ፡ በዚያም ከአይጦቹ መካከል ለየት ያለ ነገር የነበረው አይጥ አየ። የ ሚኪ ማውስ ታሪክ የተወለደበት ቦታ በዚያ ነው። አሁን ባለ ብዙ ሚሊየነር ዋልት ዲስኒ ነው። ለምን? በእጁ የሆነ ነገር ነበረው፣ እና እንደያዘውም አውቋል፣ ማድረግ እንደሚችል ያውቃል። እና እያንዳንዱ ታላቅ ስኬት የሚከናወነው በዚህ መንገድ ነው። ወንዶች እና ሴቶች በእጃቸው የሆነ ነገር ሲኖራቸው፡ ይህን ማድረግ እንደሚችሉ ያውቃሉ።

48 ፖሊዮ ሀገሪቱን በመታት ጊዜ ነው። እና፡ ነገሩን ለማጥፋት፡ ሁላችንም ሄደን እንድንከተብ ታዘዝን። ፖሊዮው በመታ ጊዜ... ትናንትና መንገድ ላይ እየነዳሁ ስሄድ አንድ ዶክተር እያዳመጥኩ ነበር፣ የሉዊስቪል ዶክተር ነው። እንዲህ አለ፦ “ከጥቂት አመታት በፊት፡ ያ ታላቅ መቅሰፍት ሉዊስቪል ሲመታ፣” አለ፡ “እኔ በነበርኩበት ሰፍራ ሰዎች ቢኖሩ ኖሮ፡ በአንድ ጊዜ አምሳ-ሰባት መተንፈሻዎችን፡ ሰዎችን አይቻለሁ፡ ሴቶች፡ ወንዶች፡ እና ልጃገረዶች ‘ፖሊዮ’ በሚባል በሽታ ሽባ ሆኑ፡ በዚህም ላይ ምንም ማድረግ አልተቻለም።” “እንደዚህ ያለ ነገር እንደገና ማየት አልፈልግም፡” አለ።

49 ሳይንስ ግን፡ “ፖሊዮ የሚባል ክፉ ነገር ካለ፡ በእርግጠኝነት እሱን የሚያጠፋው ነገር አለ” ብለው አሰቡ። ተዋጉት፣ የእሳት አደጋ ተከላካዮች፡ ቦቲ ለብሰው ወደ ጎዳና ወጡ፣ ኮፍያቸውን አውጥተው፡ ተማፀኑ፣ ተደበደቡ፣ ሁሉንም ነገር አደረጉ፣ የነፃነት በር ለመክፈት መክፈቻውን ለማግኘት እየሞከሩ ነው። እና፡ በመጨረሻም፡ ሳልክ የተባለ አንድ ክርስቲያን ሰው ክትባቱን አገኘው። ለምን? ያንዣበበ አደጋ፡ ያንዣበበ ገዳይ ስለነበረ ነው። ለሰው ልጅ ነፃነትን እንደገና የሚከፍት መክፈቻ ነበር በሆነ ቦታ ነበር፡ እና የሳልክ ክትባት ትልቅ ህክምና ሆነ። ኦህ፡ የመክፈቻው ጥቅም ብዛቱ! ክትባቱ ተመረተ፣ አሁን በዚህ ክትባት የፖሊዮ መጥፋትን እያየን ነው፣ ምክንያቱም “ያላሰለሰ፡ ጽኑ ጥረት” ስለነበረ፡ ያ ቁልፉ የሆነ ቦታ ነበር። ለመከተብ ልንጠቀምበት የምንችለው ነገር ነበር፣ እና እሱን ለማግኘት ቆርጠዋል።

50 እንደ ፖሊዮ፣ ዲፍቴሪያ፣ ፈንጣጣ፣ ቢጫ ወባ፣ ቴታነስ፣ መንጋጋ ቆልፍ፣ እና የመሳሰሉት ክፉ እስካለ ድረስም፡ ሳይንሱ፡ እነዚህን ክፉዎችን፡ ቀን እና ሌሊት፡ በእያንዳንዳቸው ላይ ክትባት እስኪያገኙ ድረስ፡ ክፉ ስለሆነ፡ የሚገድል ነገር ስለሆነ፡ ሊዋጋቸው ችሏል፡ በኃጢአት ቤት ውስጥ ለታሰረ ሰውስ የመዳን መክፈቻ ምን ያህል ይኖረው ይሆን? ሰዎችን ከዚህ ነፃ የሚያወጣ፡ የዚያ በር

መክፈቻ አለ።

51 መክፈቻ፣ ብዙ ጊዜ፡ ቁልፉን መቆለፋችሁ፡ እና፡ መክፈቻን መያዛችሁ፡ ውድ ለሆነው ሀብት ነው፣ ጠቃሚ ስለሆነ ነገር ነው፡ አለበለዚያ እንቆልፈውም። መቆለፍ በማይገባበት ጊዜ፡ ስለሱ አንጨነቅም። ዋጋ ሲኖረው ግን እንቆልፋለን! ስለዚህ መክፈቻ ብዙውን ጊዜ ለ—ለአንድ ነገር ለማሳካት ነው፣ ወይም ወደ አንድ ጠቃሚ ነገር ለመድረስ መንገድ ነው። እንግዲያውስ፡ መክፈቻው፡ የሚጠቅመው፡ ጠቃሚ የሆነውን ነገር ለመክፈት ነው።

52 አሁን ደግሞ በቅዱስ ዮሐንስ፡ ምዕራፍ 10 ላይ፡ ኢየሱስ እንዲህ ሲናገር እናነባለን፡ "እኔ የበጎች በረት በር ነኝ። እኔ በሩ ነኝ፡" **በር** አይደለም፣ "**በሩ**፣ ብቸኛው በር ነው። እኔ መንገድ፣ ብቸኛ መንገድ፣ እውነት፣ እና ሕይወት ነኝ፣ በእኔም በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም። እኔ የበጎች በረት በር ነኝ ከእኔ በፊት የመጡ ሁሉ ጠላቶች፣ ሌቦችና ወንበዴዎች ናቸው።" እርሱ የበጎች በረት በር ነው። እርሱ የመዳን በር ነው።

53 "ትድኑበት ዘንድ የሚያስፈልግበት ስም ከሰማይ በታች የተሰጠ ሌላ ስም የለም፥ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በቀር።" በኢየሱስ ስም ብቻ እንጂ፡ በቤተ ክርስቲያንም፣ በሃይማኖት ተቋም፣ በእምነት መግለጫ፡ በምንም ዓይነት ትምህርት አይደለም። መክፈቻው ያ ነው—ያ ነው። ጴጥሮስ እንዴን በጰንጤቆስጤ ቀን መጠቀሙ ምንም አያስገርምም! በዚህ በር እንዴት እንደሚገቡ ለማወቅ ፈለጉ። መክፈቻውን ተጠቀመ። እና አንድ መክፈቻ ብቻ አለች፡ ምክንያቱም አንድ በር ብቻ ስላለ። "በሩ እኔ ነኝ።" የበሩ መክፈቻም ጴጥሮስ ይዟት ነበር። እርሱም፦ "ንስሐ ግቡ፥ ኃጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ፡ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፡ የእግዚአብሔርንም ባለጠግነት ትቀበላላችሁ።" የበሩ መክፈቻ ያ ነው፡ በሩም ኢየሱስ ነው።

የፈውስ በር አንድ ብቻ ነው፡ ያ በር ኢየሱስ ነው።

54 አንዲት የሰላም በር ብቻ አለች። አዎን። "ሰላሜን እሰጣችኋለሁ።" የእውነተኛው ሰላም በር እርሱ ብቻ ነው። ሰላም አለኝ ብላችሁ ታስቡ ይሆናል። ቤት ለመግዛት በቂ ገንዘብ ታጠራቅማለህ፡ ለልጆችህ ልብስ የምትገዛበት የምትበላው ምግብ የምታገኝበት፡ በቂ ገንዘብ ልታከማች ትችላለህ፣ እንዲሁም በሰዎች ዘንድ ተወዳጅ ለመሆን በቂ ተወዳጅነት አግኝተህ ይሆናል። ሌሊት ጫማህን አውልቀህ ለመተኛት ስትዘጋጅ ግን፡ ሰላምን የሚሰጥህ አንድ ነገር ብቻ ነው። ይኸውም፡ በዚያ ሌሊት እንደምትሞት ካወቅህ፡ ሰላም አንድ ብቻ ነው፡ እርሱም፡ ሰላም የሆነው፡ ኢየሱስ ነው። እርሱ ሰላማችን ነው።

55 እርሱ ፈውሳችን ነው። "እኔ ደዌህሽን ሁሉ የሚፈውስ እግዚአብሔር አምላክሽ ነኝ።"

56 እርሱ የሰማይ በር ነው። ከኢየሱስ ክርስቶስ በቀር ሌላ በር ወይም ሌላ መንገድ የለም። እርሱ የገነት በር ነው።

57 እናም አሁን ኢየሱስ ለእነዚህ ነገሮች ሁሉ በር ነው፣ እምነትም በሩን የሚከፍት መክፈቻ ነው። አሁን፣ ኢየሱስ ለእነዚህ ሁሉ የእግዚአብሔር ተስፋዎች በር ከሆነ፣ እሱ ባጠናቀቀው ስራው ላይ ያለን እምነት በእግዚአብሔር መንግስት ውስጥ ላለው ባለ ጠግነት ሁሉ በር ይከፍታል። አያችሁት?

መክፈቻው... እምነት እሱ የገባውን ቃል ኪዳን ሁሉ የሚከፍት መክፈቻ ነው። የእምነት መክፈቻ የሚያደርገው ይህ ነው፣ በተጠናቀቀ ስራው ላይ ያላችሁ እምነት። እየተነጋገርንባቸው ያሉት መክፈቻዎች እነዚህ ናቸው።

58 እንግዲህ በዕብራውያን፡ ምዕራፍ 11 ላይ፡ የነዚህን የእምነት ጀግኖች ረጅም ዝርዝር፡ እዚህ ተጽፏል። የአንበሶችን አፍ የዘጋው፡ የ—የበሩ፡ መክፈቻ ነበር። እስር ቤቶችን የከፈተው፡ ይህ መክፈቻ፡ እምነት ነበር። የእሳትን ኃይል ያጠፋው፡ እምነት ነው፡ የእምነት መክፈቻ፡ የሰይፉን ስለት ያዳነው፣ ሙታንን ወደ ሕይወት ያስመለሰው የእምነት መክፈቻ ነው። በሕያው አምላክ ላይ የማመን መክፈቻ የሆነው፡ እምነት ነበር። ይህንን የእምነት መክፈቻ የሚይዝ፡ ይህ እጅ፣ ይህ ወንድ፣ ሴት፣ እግዚአብሔር የገባውን ቃል ሁሉ ሊከፍት ይችላል። ያ መክፈቻ ከሌለህ ግን፡ ዝም ብለህ እየተሽኮረመምክ ነው፣ በፍጹም አትከፍተውም። ይህን ለማድረግ ትታገላለህ፣ ምክንያቱም ይህ መክፈቻ...

59 ለማንኛውም በደንብ ለተሰራ መክፈቻ ሁሉ፡ በመቆለፊያው ውስጥ የብረት እጀታዎች አሉት፡ እነዚህ መክፈቻዎች እነዚያን የብረት እጀታዎችን ለማዞር የተወሰነ መዋቅር ሊኖራቸው ይገባል። እና አንድ ትንሽ የብረት እጀታ ብቻ፡ መላውን ሰርዓት ከመሰመር ውጭ ያደርገዋል።

60 ለዛም ነው፡ ወንጌልን በሙሉ የማምንበት፣ የእግዚአብሔር ቃል ሁሉ፣ የእግዚአብሔርን ኃይል የሚያነሳሳው፣ በረከቱን በሰዎች ላይ የሚያወርድ እሱ ነውና። የሚከፍተው፡ ያ የበሩ መክፈቻው ነው። ኦህ፡ እነዚህ ታላላቅ ጀግኖች፣ እነዚህ ነቢያት እና የመጽሐፍ ቅዱስ ታላላቅ ሰዎች፣ ይህ መክፈቻ ነበራቸው! ለዚህም ነው የአንበሶችን አፍ መዝጋት፣ የእሳትን ኃይል ማጥፋት፣ ከሰይፍ ስለት ማምለጥ፣ ሙታንን ወደ ሕይወት መመለስ፣ ልዩ ልዩ ተአምራት ማድረግ የቻሉት፣ ይህን መክፈቻ ስለያዙና መሠራቱን ስለሚያውቁ ነው፡ ምክንያቱም ከቅዱስ ቃል-የተወለደ መክፈቻ ነው።

61 አሁን፣ የእምነት መግለጫ መክፈቻ ይዤ የምሽኮረመም ከሆነ፣ ምን እንደሚያደርግ አላውቀውም። አንድ ሰው “ቤተ ክርስቲያናችን **ይህን** ታስተምራለች” ቢለኝ፡ እኔ ስለዚያ አላውቅም።

62 ያንን የሚያስተምር ራሱ መጽሐፍ ቅዱስ ከሆነ ግን፣ እና የእምነትን መክፈቻ በእጄ፡ ወይም በልቤ እይዛለሁ፣ እሱም “ይህ የእግዚአብሔር ቃል ነው” ይላል፡ ይህም የእሳቱን ኃይል ያጠፋል፣ ፈውሰንም ለታመሙት ይከፍታል፡ ለጠፉት መዳንን ይከፍታል። ሁሉም በስሙ ነውና፡ ወደ በሩ መቅረብ አለብኝ። “በቃልም ሆነ በሥራ የምታደርጉትን ሁሉ፡ በስሙ አድርጉት።” መክፈቻህ እምነት መሆኑን እወቅ፣ ምክንያቱም ከቅዱስ ቃል-የተሰራ መክፈቻ ነው። አሁን፣ የእምነት መግለጫ መክፈቻ ከሆነ፣ የሐይማኖት ተቋማት መክፈቻ ከሆነ፣ ምን እንደሚያደርግ እኔ አላውቅም። ከቅዱስ ቃል የሆነ መክፈቻ ግን፡ ይከፈታል፡ ምክንያቱም እግዚአብሔር ተናግሯል። አሁን፡ ኦህ፡ የእሳቱን ኃይል እና ሁሉንም ነገር ማቆም መቻላቸው፡ ምንም አያስገርምም፡ መክፈቻው ነበራቸው።

63 እግዚአብሔር ይሄን አድርግ ብሎ ከነብያት ለአንዳቸው በሚያሳያቸው ቀዳሚዋ ምልክት፡ አንዳች የሚያስቆማቸው አልነበረም። አንዳንድ ጊዜ ከእኔ ጋር እንደሚያደርገው ማድረግ አያስፈልገውም፣ ደጋግሞ እየደበደበኝ፣ ምናልባት

በእናንተም (እንዳይሆንባችሁ ተሰፋ አደርጋለሁ)፣ ግን ያለማቋረጥ፣ “ሂድ እና ይህንን አድርግ” ይለኛል፣ ከዚያም ሰሰናከል፡ “ከዚያ ሂድ **ያንን** አድርግ፡” እና “ተመለሰ እና እንደገና አድርግ፣ በትክክል አልሰራኸውም።” ትንሽ የአድርግ ምልክት ብቻ! በቃ፡ መንፈሱ፣ “ይህ ማድረግ ትክክለኛው ነገር ነው” በማለት ማድረግ ያለባቸው ነገር እንደሆነ ይሰማቸዋል፡ አንዳችም የሚያሰቆማቸው አይኖርም። ወንድሜ፡ እ—እ—እነሱ’ኮ የአንበሶችን አፍ ዘጉ፣ ከሰይፍ ሰለት አመለጡ፣ እሳቱን አጠፉ፣ ሁሉንም ነገር አደረጉ። ከእግዚአብሔር በሆነች ትንሽ የአድርግ ምልክት፣ ምክንያቱም መክፈቻው፡ ታላቁ እምነት በእጃቸው ይዘዋል! ነገሮችን ለእግዚአብሔር ያደርጉ ነበር ምክንያቱም አንዳችም የሚያሰቆማቸው አይኖርም። ኦህ፡ እንዴት ያለ ክብር ነው!

64 አንድ ጎልማሳ በአንድ ወቅት ወደ አንድ ወንድም መጣ፡ እርሱም ቅዱስ የሆነ ሽማግሌ የእግዚአብሔር ነብይ ነበር። ይህ ሰው ሰለ እግዚአብሔር ቸርነት፡ ሰለ እግዚአብሔር ምንነት፡ ደጋግሞ ሲመሰክር ይሰማዋል፡ ሰለ ክርሰቶስ ምንነት ሲናገር፡ ያለማቋረጥ ሲመሰክር ይሰማዋል፡ ሁልጊዜም ይናገር ነበር። በመጨረሻም፣ ይህ ወጣት ለአገልግሎት ሊሾም ሆነና፣ ወደ እኚህ ጠቢብ ሽማግሌ በመሄድ፣ እንዲህ አለው “ጌታዬ፡ አንድ ጥያቄ ልጠይቅህ እፈልጋለሁ፡” አለው።

እሱም “ጠይቅ፡ አንተ ጎበዝ፡” አለው።

65 “በእውነት ክርሰቶሰ እንደምትናገርለት ለአንተ እንዲሁ ነውን፡” በማለት ጠየቀው?

66 እርሱም መለሰ፡ “ትንፋሼ ከምትገልጸው በላይ እሱ ለእኔ እንዲሁ ነው!” ይኸው ነው። ምን ነበር? መክፈቻው አግኝቶ ነበር።

67 ከዚያም፡ ይህ ወጣት በዚያ ነገር ላይ፡ “እነዚህን ነገሮች ካረጋገጥክ፡ እና ልክ እንደ አንተ እውን መሆናቸውን ከነገርከኝ፣ እንግዲያውስ ይህንኑ ኢየሱስን፡ በተመሳሳይ እውነት እሱን ማወቅ እፈልጋለሁ።” ይህ ምን ነበር? ይህ ሽማግሌ መክፈትም መዝጋትም የሚችልበት፡ ቁልፍ መያዙን ተገነዘቧል።

68 ታውቃላችሁ፡ የሚቆልፈው መክፈቻ፡ እንዲሁ፡ ይከፈታል። አያችሁ? መፍታት ወይም ማሰር እንችላለን። እውነት ነው። የሚቆለፈው ተመሳሳይ መክፈቻ፡ ይከፈታል። የሚከፍተው መክፈቻ፡ መቆለፍ ይችላል። ይህም ትክክል ነው፣ አያችሁ፣ ምክንያቱም በሁለቱም መንገድ ይሰራል። ቤተ ክርሰቲያኒቱ ለዚህ ያላትን ራዕይ በማጣቷ እንዴት ያሳዝናል! እንደ ዛሬው ሁሉ፡ ቤተ ክርሰቲያን እራሷን ለሃይማኖት መግለጫ ሸጣ፡ አሁን ለአንድነትን መጥራቷ እንዴት ያሳዝናል።

69 ታላቁ የሮማውያን የሰልጣን ተዋረድ እና ሌሎቹ ሁሉ አሁን ይሰባሰባሉ፡ እዚያም አንዳንድ ፕሮግራሞችን ይለዋውጣሉ። እኔ አይለወጡም ብዬ አሰቤ ነበር፡ ይሁን እንጂ፡ እንዲሁ ያደርጉታል። ለእያንዳንዱ ቄሰ የጳጳሰ ሰልጣን ይሰጠዋል፣ የ—የትም ይሁን የት፡ ወዘተረፈ። ቤተ ክርሰቲያን ከቃሉ ይልቅ ራሷን ለዶግማ መሸጧ፡ እንዴት ያሳዝናል። አያችሁ? መክፈቻውን የጣሉት እዚያ ነው፡ እዚያ ላይ ነው። ዛሬ በሰዎች መካከል ታላላቅ ተአምራትን እና ምልክቶችን የማናየው በዚህ ምክንያት ነው፡ እንደ ቀድሞው፡ መክፈቻውን

ጠፍቶባቸዋል! አዎን፡ በሩን ያውቁታል፡ በሩ እንዳለ ያውቃሉ፡ ግን የሚቀጥለው ነገር በሩን ለመክፈት መክፈቻው ነው። ባለጠግነት ከበሩ በስተጀርባ ነው። ከማያምኑ ሁሉ፡ ከይናቸው ተሰውሮ፡ ተዘግቶባቸዋል። እምነት ያለው እና የእምነትን መክፈቻ የሚወስድ፡ አማኝ ግን፡ እነዚህን በሮች መክፈት ይችላል። አዎን፡ ወዳጄ።

70 በአንድ ወቅት፣ ከጥቂት ዓመታት በፊት፣ ወደ አፍሪካ ጥሪ እንዳለው የሚሰማው አንድ ወንድም ሚስዮናዊ ነበር። ወጣት ነበር፡ ሰባት ወይም ስምንት ዓመት ገደማ የሆናቸው፡ ሁለት ልጆች፡ እና ሚስት ነበረው፡ በጣም ቆንጆ ሴት ልጆች፡ ነበሩት። እናም ይህ ወጣት ይህንን ጥሪ ችላ ማለት አልቻለም። አ—አገልጋይ ነበር፣ በአገሪቱ ውስጥ ጥሩ ቤተክርስቲያን ነበረው። ግን ይህን ጥሪ በቀላሉ ችላ ማለት አልቻለም፡ "ወደ አፍሪካ መሄድ ነበረበት"። ቀንና ሌሊትም፡ ጸለየ። ወደዚያ መሄድ አልፈለገም። እግዚአብሔርም፡ "መሄድ አለብህ" ይለው ነበር! እና በመጨረሻ፡ ወደ አንድ የለውጥ ነጥብ መጣ፡ ማለት፡ መሄድ ነ—ነበረበት!

71 ወደ ቤተክርስቲያኑ የሚስዮን ቦርድም በመሄድ፣ "እግዚአብሔር ወደ ሚሽን መስክ፣ ወ—ወደ ሮዴዢያ ጫካ ዘንድ እንድወጣ ይፈልገኛል" አላቸው። እና ይህ ጫካ ከጸሐይ ሙቀት ጋር በወባ፣ በትኩሳት፣ በቸነፈር እና በሰጋ ደዌ የተሞላ ነው፣ በዚህ ጫካ ውስጥ እድሜ ልኩን ሊ.... ሊኖር ባለበት በዚህ ጫካ ውስጥ፡ ሁሉም አይነት በሽታዎች ነበሩ። ቤቱንና ያለውን ሁሉ ሸጠ። ስለዚህ የሚስዮናውያን ኮሚቴው ሊፈትኑት ፈልገው፡ "በእርግጥ እርግጠኛ ነህን፡" አሉት?

እሱም "እርግጠኛ ነኝ፡" አለ።

72 እነርሱም እንዲህ አሉት፡ "ጌታዬ፡ በዚህ መልኩ ግን አሰበህበታል፡ ሁለት ቆንጆ ሴት ልጆች አሉህ፡ እንዲሁም እጅግ ተ—ተወዳጅ ወጣት ሚስት ይዘሃል፡ አንተ ይሄን ካልክ... ለምን ብቻህን ሄደህ እንዴት እንደሆነ አይተህ አትመለሰም? "

73 እርሱም፡ "አይ፣ ጌታ ነግሮኛል። ኦህ፣ በጣም እውነት ነው!" እነሆ፡ "ጌታ ጠርቶኛል። እኔ—ቤቴን መልቀቅ አልፈልግም፣ ቤተክርስቲያኔንና ህዝቤን ትቼ መሄድ አልፈልግም፣ ነገር ግን ወደዚያ ጫካ እንድሄድ ጌታ ጠርቶኛል" አላቸው።

74 እነርሱም፡ "ጌታዬ፥ ትናንሾቹ ሴቶች ልጆችህ ቢጫ ወባ ወይም ትኩሳት ተይዘው፡ በአንድ ሌሊት፡ ሊሞቱ እንደሚችሉ ታውቃለህን? " ልጆቻቸውን፣ ትንንሽ ልጆቻቸውን ያጡ የተለያዩ ሰዎች ጠቀሱለት፣ ክትባት ያልተገኘባቸው በሽታዎች ወዳሉበት፡ ወደዚያ እነዚህን መውሰድህ ብለው ተናገሩት። አሉትም፡ "ለምጹን አሰበው፡ ውዷ ባለቤትህ እና ሁለቱ ሴቶች ልጆችህ ለምጽ ቢይዛቸውሳ፥ ልትታገሰው የሚገባው ያንን ንዳድ ጸሐይስ ሌሎችስ።" "ልጆችህን እና ሚስትህን በእንደዚህ አይነት ቦታ የመውሰድ፡ አደጋው አያስፈራህም፡" አሉት?

75 እናም ያ ሚስዮናዊ ቆሞ፣ ያ ወጣት፣ እንባው በጉንጮቹ ላይ ይንከባለል ጀመር፣ እናም ዘወር አለና፣ እንዲህ አለ፡ "ወንድሞቼ! የእግዚአብሔር ጥሪን

በተመለከተ፣" እርሱ፡ "ወደ አፍሪካ እንድሄድ እግዚአብሔር ከጠራኝ፣ ልጆቼና ቤተሰቤ በዓለም ላይ ካሉት የዓለም ክፍሎች ይልቅ በአፍሪካ ውስጥ ደህና ይሆናሉ" አላቸው። አሜን። ምን ነበር? የጥሪው መክፈቻ ነበረው፣ በተናገረው ነገር ላይ እምነት ነበረው። ኦህ፣ እንዴት ያለ አስደናቂ መልስ ነው ብዬ አስባለሁ! ይህን ለመጀመሪያ ጊዜ በሰማሁ ጊዜ ልቤ በጣም ዘለለ። አያችሁ፡ "ልጆቼ በለምጽ እና በቸነፈር እና በሁሉም ነገር መካከል፣ ወደ አፍሪካ እንድሄድ እግዚአብሔር ከጠራኝ፣ ምድር ላይ ካሉት ከየትኛውም ቦታ ይልቅ ደህና ይሆናሉ።" መክፈቻውን ይዞ ነበር። ዋናው ነገር እሱ ነው።

76 መክፈቻው ከያዝክ፡ ምንም አያስፈራህም፡ አትጠራጠርም፡ ምንም ጥያቄ የለህም። የሌላ ሰው አስተያየት አያስፈልግህም፡ በእርግጠኝነት ታውቀዋለህ። በእጅህ ውስጥ አለህ፡ ምን ማድረግ እንዳለብህ ታውቃለህ። አሜን። በውጤቱ ላይ እርግጠኛ ትሆናለህ፡ በሩ እንደሚከፈት እርግጠኛ ነህ። የብረት እጀታዎቹ ፈትሸሃቸው ትክክለኛ ሆነው አግኝተሃቸዋል፡ መክፈቻውን ስትስካበት በሩ እንደ ብልጭታ ይከፈታል።

77 ኦህ፣ ቤተክርስቲያን መክፈቻዎችን ቢኖሯት! ቤተ ክርስቲያን ያንን የእምነት መክፈቻ ብቻ ቢኖራት፣ ደዌዎች፣ መቅሰፍቶች፣ ሁኔታዎችን ሁሉ፣ መክፈት እንችል ነበር። ይህን መክፈቻ መያዝ ከቻልን ይህ ሁሉ ሊከፈትልን ይችላል። ይህ ሰው የጥሪው መክፈቻ ነበረው።

78 ከፈቀዳችሁልኝ የግል ምስክርነት ልስጣችሁ። የዛሬ አስራ አምስት፡ ወይም አስራ ሰባት አመት፡ ገደማ፡ ጌታ በዚያ በወንዙ ዳርቻ በተናገረኝ ጊዜ፡ አሁን እናንተ በምታዩት ስዕል በዚያ በእሳት ዓምድ መልክ መጥቶ፡ ሲናገረኝ እንዲህ እንዳለ አስታውሳለሁ፡ "ይህንን መልእክት ለዓለም ሁሉ ታደርሳለህ።"

በግሪን ሚል ውስጥ ሲያናግረኝም ትዝ ይለኛል።

79 ሄጄ ለፓስተሩ ነገርኩት፡ እርሱም አለኝ፡ እንዲህ በማለት፡ "ቢሊ፡ በዚያ ሌሊት ምን በልተህ ነበር? ቃዥተህ ነበር።" አለኝም፡ "ሂድና ወደ ሥራህ ተመለስ። ለሕዝብ አገልግሎት ትሠራለህ፣ ጥሩ ሥራ አለህ፣ ወ—ወደ ሥራህ ተመለስ፣ ልጄ።" "የሆነ ነገር በልተሃል። አቃዥቶህ ነው፡" አለኝ። ያ በፍፁም አላስተጓጎለኝም!

80 የፈውስ አገልግሎትን ማከናወን በጀመርኩበት ጊዜ፣ በዚያን ቀን ጠዋት የሰበክሁትን መልእክቴን ብዙዎቻችሁ አስታውሱ፡ **ዳዊት ጎልያድን ለመግጠም እንደ ሄደ**፡ ብዬ ሰብኬአለሁ።

81 እንዲህ አሉኝ፡ አለኝም፡ "በዚህ ዘመናዊ የሳይንስ ዘመን፡ ሁሉም አይነት የህክምና ምርምር ባለበት፡ ምርጥ ዶክተሮች ባሉበት፣ ቤተክርስትያን ስለ መለኮታዊ ፈውስ እና እነዚያን ነገሮች ከብዙ፡ እና ከብዙ ብዙ ከአመታት በፊት በሰራችበት በዚህ፣ እንደዚህ አይነት ታላቅ ግዙፍ ነገር እንዴት ትገጥማለህ? በሜቶዲስት፣ እና ባፕቲስቶች፣ እና በፕሪስባይቴሪያን፣ እና በሁሉም ፊት፣ ጴንጤቆስጤዎች እንኳ ሳይቀር ያንን ከረጅም ጊዜ በፊት ረስተውት፡ ወደ ሃይማኖት መግለጫ በተመለሱበት ጊዜ፡ በፊታቸው እንዴት ትራመዳለህ? ያለ ሓይማኖት ተቋም ድጋፍ፡ ወይም ሌላ የሚደግፍህ ነገር ሳይኖር ይህን ሁሉ እንዴት ትጋፈጣለህ? ምን ታደርጋለህ፡ ቢል? " በእጄ መክፈቻ ይዤ ስለነበር፡

ይህ፡ ምንም፡ አላሰደናገረኝም! አልኳቸው… “ማንም አያምንህም። ማድረግ አትችልም። ማንም አያምንህም፡” አሉኝ።

82 እኔም፣ “ምንም ግድ የለኝም። አንድ ነገር እርግጠኛ ነኝ፥ እግዚአብሔር ጠርቶኛል፡ እግዚአብሔር ስለጠራኝ መሄድ አለብኝ።” መክፈቻውን ያዝኩት። ጠራኝ፣ አሳየኝ፣ ሰለ ጉዳዩ ነግሮኛል፣ እሱ ባዘዘኝ ጊዜ መገኘቱን አይቻለሁ፣ እና መክፈቻውም እዚያ ነበር!

83 ፓስተሩ እንዲህ አለኝ፣ “የሰባተኛ-ክፍል ትምህርት ይዘህ፣ ለነገስታት እና ከበርቴዎች ትሰብካለህን ትጸልያለህን!”

እኔም አልኩት፡ “እንደ ቃሉ ነው!”

84 ባለፈው ዓመት በዚህ ጊዜ፣ ወይም ከአንድ ወይም ከሁለት ሳምንት በፊት፣ ወደዚህ ወደ ቤተክርስቲያን መጥቼ ጌታ እግዚአብሔር ራእይን እንደ እንዳሳየኝና፣ ለአደን ጉዞ እንደምወጣ፡ እ—እና ወደምሄድበትም ነገርኳችሁ፡ ቀንዶቹ አርባ-ሁለት-ኢንች የሚያህል አንድ እንሰሳ አድናለሁ ብያችሁ ነበር። እና ይህንን እንሰሳ አድኜ ሰመለሰ የሚገጥመኝ (የት እንደሚተኛ፡ በምን አቅጣጫ እንደሚገኝ)፡ በመመለስ ላይ የሲቨር ግሪዝሊ-ድብ እገላለሁ ብያችኋለሁ። እና ወደዚያ አካባቢ ሄድኩ እና፡ ስለ ጉዳዩ ለአንድ ሰው ነገርኩት፡ እና እንዲህ አለ፡ “እንዲህ አይነት እንሰሳ እኔ አላውቅም። ስለ ግሪዝሊ ድብ፣ አንድም አይቼ አላውቅም።”

እኔም “ግን እዚህ በሆነ ሰፍራ ውስጥ ይኖራል፡” አልኩት።

85 ስለዚህ እንዲህ አለ፡ “ድብ ወዳለበት አካባቢ እንኳን አንሄድም። የምንሄደው ከጫካው ጫፍ ርቆ፡ አውራ በግ ወዳለበት ነው።” ከዚያ፡ ከእሱ ጋር ሄድኩኝ።

86 በሁለተኛውም ቀን፣ በዚያው ሰፍራ፣ ልክ ጌታ በተናገረበት፣ እንሰሳው በዚያ ነበረ። ስለዚህ እንሰሳውን ለመያዝ ከሄድኩ በኋላ፡ ቆዳውን እና ቀንዶቹን እና ሁሉንም ነገር፡ እያሰወገድን ሳለ፡ እንዲህ አለኝ፡ “አንድ ጥያቄ ልጠይቅህ እፈልጋለሁ። ከሶስት ቀን በፊት፡ ከ—ከካምፑ ሰንወጣ፡ ይህን አውሬ በጥይት መትተህ ሰትመለስ፡ በመንገድ ላይ፡ ‘ሲልቨር-ቲፕ ግሪዝሊ ድብ ልትገድል’ እንደሆነ ነግረኸኝ ነበር።”

አልኩትም፡ “**ይህ የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ነው**!”

87 እንዲህ አለ፡ “አልጠራጠርም፡” አለኝም፣ “ምክንያቱም ወንድሜ የሚጥል በሽታ ነበረበት፣ እናም አንድ ጊዜ እዚህ በመጣህ ጊዜ፡ በፊት በህይወትህ አይተኸው አታውቁም ነበር፡ አንድ ነገር እያደረግሁ ሳለሁ ይህ ልጅ እንደሚፈወስ ነግረኸኝ ነበር። ተፈወሰም።” እንዲህ አለ፣ “አሁን፡ ነገር ግን፡ ወንድም ብራንሃም ሆይ፣ አንድ ጥያቄ ልጠይቅህ እፈልጋለሁ፣” አለ፣ “ከዚህ እስከዚያ ተራራ እስከ ጫካው ጫፍ ድረስ፡ እነዚያ ፈረሶች ወደሚገኙበት ይታየኛል። እና እዚያ ምንም ነገር የለም። የሣር ክምር የለም፡ ድንጋይ የለም፡ ምንም ነገር የለም።” ከዛፉ ባሻገር፡ ወይም ካዛፉ አንድ ማይል ወይም ከዚያ ርቆ፡ ሁለት ኢንች የሚያክል ቁመት ያለው፡ ካሪቦው የሚመገበው ሳር ነበረ። “ታዲያ ድቡ የት ይሆን ያለው፡” ጠየቀ?

88 እኔም፣ “እግዚአብሔር ያህዌ-ጂሬህ ነው። እዛ ድብ እንደሚኖር ከተናገረኝ፡ እዚያ ይኖራል።

89 ከተራራው ወርደን፣ ግማሽ ማይል ያህል፡ ወደፊት በተጠጋን ቁጥር፣ “ወንድም ብራንሃም፡ ያ ድብ የሚታይበት ጊዜ አሁን ነው፡” ይለኛል።

“አትጨነቅ፡ እዚህ እናገኘዋለን፡” አልኩት።

90 እና ፈረሶቹ ካሉበት አምስት መቶ ያርድ ርቀት ላይ ሰንደርስ፣ ከከባዱ ቀንዶች እና በጀርባችን ካሉት ነገሮች ምክንያት እንደገና ማረፍ ነበረብን። ዳግመኛ ዞር ብሎ ተመለከተ፣ እና ፊቱን እያየኝ፣ በልቡ ውስጥ የሚደነቅ ይመስል ፊቱን አየሁት። አያችሁ፣ እዚያ እንደሚኖር **ተሰፋ** አድርጎ ነበር፣ መክፈቻው ግን አልነበረውም።

91 ነገር ግን በዚህ በዚያም ብሎ፣ በእግዚአብሔር ቸርነት፣ ከቶ እያሳፍረኝም። ሲልቨር-ቲፕ ድብ እንደሚኖር ሲነግረኝ፡ መክፈቻው ነበረኝ። ለአንድ አፍታ አልተጠራጠርኩም፡ በፍጹም። ወደ እሱ ዞርኩና፣ “በድ፡ እናገኘዋለን፡” አልኩት። እና ልክ እንደዞርኩ፣ ድቡ እዚያ ነበር [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ—አርታዒ።] ከፊት ለፊታችን ነበር፣ በግማሽ ማይል ርቀት ላይ።

92 ቢኖክዮላውን ወረወረና፣ እንዲህ አለ፡ “ቢሊ፣ ትልቅ ሲልቨር-ቲፕ ነውና፡ እርዳኝ!”

93 አያችሁ፣ መክፈቻው፣ ራዕዩ፣ የጌታ ቃል፣ ምንም የሚቀይረው ወይም የሚያቆመው የለም። ቤተ ክርስቲያን ዛሬ ማታ የሚያስፈልጋት የቀለም ትምህርት አይደለም። ዛሬ ማታ ቤተ ክርስቲያን የሚያስፈልጋት የሐይማኖት ተቋም አይደለም። ዛሬ ማታ ቤተ ክርስቲያን የምትፈልገው የሃይማኖት መግለጫ አይደለም። ቤተ ክርስቲያን ዛሬ ማታ የሚያስፈልጋት የቅዱስ ቃል መክፈቻ የሆነው፡ በሩ ነው። ማለት፡ ክርስቶስ በር ነው፡ እርሱም ቃል ነው። በሕያው እግዚአብሔር ቃል ላይ ያለ እምነት ሁሉንም በሮች ይከፍታል።

እግዚአብሔር ሆይ፡ መክፈቻ ሰጠን። መክፈቻውን ሰጠን።

94 ዕብራውያን፡ ምዕራፍ 12 ላይ፡ እንዲህ ይላል፡ “እንደ ደመና ያሉ በዙሪያችን ታላላቅ ምስክሮች እንዳሉን አይተን፡ ሸክሙን ሁሉ፡ በቀላሉ የሚከበንን አለማመንን እናስወግድ።” “ኃጢአት” ይላል፣ **ኃጢአት**፡ ደግሞ “አለማመን” ነው። አያችሁ? ኃጢአት አንድ ብቻ ነው፡ እርሱም አለማመን ነው።

95 **ኃጢአት** ማለት “ምልክቱን መሳት” ማለት ነው። ተኩሳችሁ፡ ዒላማውን እንደመሳት ማለት ነው፡ ጠመንጃችሁን ማረም አለባችሁ፡ አያችሁ፡ ምክንያቱም የተዛባ ነገር አለ። ምልክቱን ስታችኋል። አያችሁ፣ ተመለሱና እንደገና ሞክሩ። እሺ? ዕላማውን ስለሳታችሁ፡ መመለስ አለባችሁ ማምለት ነው። ክርስቲያን መሆን ፈልገህ፡ የቤተክርስቲያን አባል ወደ መሆን ስትሄድ፡ ምልክቱን ስተኸዋል። ክርስቲያን መሆን ፈልገህ፡ እና “በአብ፣ ወወልድ፣ ወመንፈስ ቅዱስ” ስም ስትረጭ፣ ኢላማውን ስተሃል። ብትመለስ ይሻልሃል። ዒላማውን አታገኘውም። እንደ ዓለም፡ ትበታተናለህ። ፍጹም በመስመርህ የሚያቆይህ አንድ ነገር ብቻ አለ፣ እርሱም ቅዱስ ቃል ነው፣ መጽሐፍ ቅዱስ፣ ቃሉ ነው። ምክንያቱም፡ ሰማያትና ምድር ያልፋሉ፣ የእግዚአብሔር ቃል ግን አያልፍም።

96 ስለዚህ፡ መክፈቻ ያዙ፣ በቃሉ ላይ እምነት! ባመንከው እምነት ሁሉ፣ አንድም ጥርጣሬ ባይኖርህ፣ በፊትህ ያለውን በር ሁሉ እና እግዚአብሔር ለአንተ ያለውን በረከት መክፈት ትችላለህ። መክፈቻው እንዲኖረን እግዚአብሔር ይርዳን፡ ጸሎቴ ነው። አሁን ለጸሎት ቃል አንገታችንን ዝቅ እናድርግ።

97 የሰማይ አባታችን፣ መዳናችንን ለመክፈት ቁልፍ ስለሰጠኸን በዚህ ምሽት እናመሰግናለን። ጌታ ሆይ፡ ስለ መዳናችን፡ እና እስካሁን ልንጠቀምበት ስለቻልነው መክፈቻ፡ እኔ—ለዛ አመሰግንሃለሁ። ነገር ግን፡ አምላክ ሆይ፡ እምነትን ሰጠን፡ በመጽሃፍህ የተፃፉት ቃላቶች ሁሉ ትንንሽ ዘንጎች ናቸውና፡ ይህ ኢየሱስ የተባለው መክፈቻም... ይህ በር፡ ማለቴ፡ ኢየሱስ የተባለው፡ እና እምነት የተናለው፡ መክፈቻ፣ ቃል ሁሉ ይዳሰሳል፣ ይከፍታልም። ትንሿን ዘንግ ያንቀሳቅሳታል እኛም ወደዚህ በረከት መግባት እንችላለን። የሰማይ አባት ሆይ፣ እምነታችንም እንዳይጠፋ፣ በእግዚአብሔር ተስፋዎች ላይ እምነት እንዲኖረን፣ ለአንተ እና በዙሪያችን ላሉ ሰዎች አገልግሎት እንድንሰጥ፡ መክፈቻዎቹን ሰጠን።

98 ስለ አለማመናችን ኃጢአት ሁሉ ይቅር በለን፣ ጌታ ሆይ፣ የአንተ እንድንሆን እርዳን። አሁን ወደ ጌታ እራት ማዕድ እንቀርባለን፣ እና ወደ አንተ፣ የሰማይ አባት፣ በደላችንን ሁሉ ይቅር እንድትል፣ በእግዚአብሔር ማዕድ ዙሪያ ወዳለው የኅብረት ደስታ እንድንገባ እጸልያለሁ። በኢየሱስ ስም እንጠይቃለን። ኣሜን።

99 ወንድሜ፣ እህቴ፣ የመንግሥቱ መክፈቻ፣ የበሩ መክፈቻ፣ የመዳን መክፈቻ ካገኛችሁ፣ በሮቹን እንድትከፍቱለት እና ኢየሱስ እንዲገባ እግዚአብሔር ይርዳችሁ። ይህ እ—እጅግ የምትፈልጉትን ይሰጣችሁ።

100 አሁን፣ ስለ ቁርባን ማንበብ ከመጀመራችን በፊት፣ አንድ ነገር ልናገር ምክንያቱም ስለ ቁርባን ስለሆነ ነው። እናም ወደዚህ መሠዊያ ስንመጣ፣ ለመምጣት አንድ መንገድ ብቻ አለ፣ ይህም፡ በእጃችን የእምነት መክፈቻ ሲሆን ነው፡ ይህ ኃጢአታችን እንደተሰረየልን እንድናውቅ ያደርገናል። ኃጢአታችን ይቅር እንዳለን የምናውቅበት፡ ይህን በር ለመክፈት መክፈቻ ከሌለን፡ ወደ ጌታ ማዕድ መምጣት የለብንም። ምክንያቱም፡ ሳይገባው የሚበላና የሚጠጣ ሁሉ፡ የጌታን አካል መለየት ሳይችል የሚበላ፡ በራሱ ላይ ፍርድ ይበላል ይጠጣልምና። እንግዲህ፡ እውነት ነው።

101 ዛሬ ብሔራዊ የጌታ እራት ቀን እንደሆነ ሁላችንም እናውቃለን። ይህ ቀን ሁሉም አብያተ ክርስቲያናት የጌታ እራት የሚያደርጉበት ቀን ነው። በመላ ሀገሪቱ ብሔራዊ የጌታ እራት ቀን ነው። ከመውሰዳችን በፊት ስለ ጌታ እራት አንድ ወይም ሁለት ቃል መናገር ተገቢ ነው ብዬ አሰቤ ነበር፣ ፓስተሩ፡ ፈቃደኛ ከሆነ፡ በጌታ ማዕድ ስነ—ሥርዓት ላይ የሚነበቡትን ቅዱሳን ቃላት ያዘጋጃል። አሁን፣ ይህ የጌታ እራት... ደህና፣ አሥር ደቂቃ ያህል ብቻ ነው የምወስደው።

102 ልንወሰደው ያለነው ይህ የጌታ እራት ትምህርት፡ ከየትኛውም የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት በበለጠ አከራካሪ ጉዳይ ሆነ ቆይቷል። በጥንቷ ቤተክርስቲያን ከመጀመሪያዎቹ አለመግባባቶች መካከል አንዱ... ይህ ጉዳይ ነው። እና ዛሬ ፕሮቴስታንቶች፣ እንደ ኤጲስቆጶሳውያን እና ሜቶዲስቶች፣ እና ብዙ የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት፡ ትንሿን የጌታ እራት ዳገት

ማለፍ ከቻሉ፣ ካቶሊክን ይቀበላሉ፣ የሮማ ካቶሊክን አስተምህሮ በደስታ ይቀበሉታል። ነገር ግን ካህኑ አግብቶ አገልጋይ መሆን እንዳለበት ይስማማሉ፡ የካቶሊክ ቤተክርስቲያን በስብሰባዎቻቸው እና ኮንፈረሶቻቸው ላይ ብዙ ጊዜ ይህንን ተቀብላዋለች። ተስማምተውበታል። እናም በተለያዩ ጸሎቶች፡ እና በብዙ ነገሮች ተስማምተዋል፡ የፕሮቴስታንት ቤተክርስቲያንም ትቀበለዋለች። ስለ ካቴኪዝም እና ነገሮች፣ እዚህ እና እዚያ ያሉ ትናንሽ መሠዊያዎች፣ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ያንን ለመቀበል ዝግጁ ነች። ወደ ቁርባን ሲመጡ ግን፡ ያኔ ሁሉም ነገር ውድቅ ይሆናል። ታሪክ ያነበበ ሰው ይህን ያውቀዋል። ግን፣ በእርግጥ፣ በእኔ አስተያየት፣ እኔ ይህን ከመቀበሌ በፊት፡ ከ—ከኔ በፊት ብዙ ነገሮችን ማስወገድ ይጠበቅባቸዋል፡ አያችሁ፡ ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም።

103 ነገር ግን ለካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን አንድ ነገር እንድትናገሯት እፈልጋለሁ። በመጀመሪያ፡ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን፡ የጴንጤቆስጤ ቤተ ክርስቲያን ሐዋርያዊት እንደነበረች ታውቃላችሁ? በትክክል ነበረች! የቤተክርስቲያኑ መጀመሪያ ላይ ነበረች። እና የት እንዳሉ አ—አይታችኋል፣ ያለማቋረጥ ቃሉን ትተው ስለ ዶግማዎችን ሲያወጉ ነበር።

104 እና የጴንጤቆስጤ ቤተክርስትያንም ወደፊት መቶ አመት የሚኖራት ከሆነ፣ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን አሁን ካለችበት መንገድ ይልቅ፡ ከመጽሐፍ ቅዱስ በጣም የራቀች ትሆናለች።

105 የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ከዚህ ለመራቅ፡ እጅግ ብዙ መቶ አመታት ፈጅቶባታል፡ ከጥንታዊቷ ቤተ ክርስቲያን፡ እስከ የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ማደራጀት ለመሸጋገር፡ ሶስት መቶ ዓመታት ፈጀባት። **ይህንንም** እየወሰዱና እየቀነሱ፣ **ይህን** እያነሱ እየጨመሩ፣ ጣዖታትን አምላካዊ ጣዖታትን እያመጡ፡ **ይህንን** እየቀነሱ **ያንንም** እየጨመሩ፡ በክርስቲያኖች ምሰል እና መሳይ ነገሮችን በመተካት፡ አሁን ወደደረሱበት፡ የሮማ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ሁኔታ እስኪደርሱ ድረስ፡ ብዙ ሲያመቻምቹ ቆይተዋል።

106 እና የጴንጤቆስጤ ፕሮቴስታንት ቤተክርስቲያን ከ—ከኖረችባቸው ሃምሳ አመታት፡ እና ከጀመረበት የወደቀበት በማየት፡ የዛሬ መቶ አመት፡ ከካቶሊክ ቤተክርስቲያን የባሰ ሁኔታ ላይ ትገኛለች። እውነት ነው። ይህ ጠንካራ አባባል ነው፡ ግን ከየት እንደወደቁ ተመልከቱ። ፈጥነው ድርጅት ወደ መሆን ገቡ፡ **በዚህ** እና **በዚያ**፡ እና በሌሎች ነገርችም ወደ ማመቻመች ደረሱ። እና ወደዚያ ሄዱ፡ አያችሁ፡ ወደ ኋላ ተመልሰዋል።

107 ነገር ግን **የጌታ እራት** ግን፡ "የጌታ መክሰስ፡" ይባላል። አሁን፡ ብዙ ሰዎች፡ ጠዋት ላይ መውሰድ ይፈልጋሉ። መጽሐፍ ቅዱስ **ቁርስ** ነው አላለም። ታዲያ ዛሬ ሰዎች፡ "የጌታ እራት" ይሉታል፡ እንጂ አያደርጉትም። **መክሰስ**፡ የሚለውን፡ ቃሉን አውጥተውታል፡ "እራት" ብለው ጠሩት፡ ከንቱነት። መክሰስ!

108 አሁን፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ዘመን ሁል ጊዜ ያከራክር ነበር፣ ያኔ አከራካሪ ነበር። ሰዎች የጌታን መክሰስ በተሳሳተ መንገድ ተረድተውታል። ወደ ማዕድ በመጡ ጊዜ፡ ጳውሎስ ለእነዚህ የቆሮንቶስ ሰዎች እንደነገራቸው፡ በጌታ ማዕድ መጥተው ይሰክሩ ነበር። አያችሁ፣ ያኔም በትክክል አልተረዱትም። "መብላት ከፈለጋችሁ፡ በቤታችሁ ብሉ፡" አላቸው።

109 ሌላው ነገር፡ በይዘቱ፡ የተሳሳተ ግንዛቤ መፈጠሩ ነው። ኃጢአተኞች፡ እና በኃጢአት ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች፡ የጌታ እራት ሊወስዱ ይመጣሉ። በተሳሳተ መንገድ ተረዱት። አንድ ሰው ከእናቱ እየኖረ፣ የእንጀራ እናቱ ያገባ ሰው፡ እናም ቤተክርስቲያኑ ስለ ጉዳዩ ተናግራለች፣ ይሁን እንጂ ማዕድ ፊት ቀርቦ የጌታ እራት ይወስድ ነበር።

110 በመካከላቸውም መለያየት ነበር፣ እና አሁንም የጌታ እራት መውሰዳቸው ግን ቀጠሉ። እንዲህም አላቸው፡ "እንደሌሎች አሕዛብ እንደምትመላለሱ አውቃለሁ። ከ—ከኬፋና ከሌሎችም ጋር፡ እንደ ሆነ፡ በ—በእናንተ መካከል ጠብ አለ።" "እናንተ እንደሌሎች አሕዛብ ትመላለሳላችሁ፡" አላቸው። አያችሁ፡ በተሳሳተ መንገድ ተረድተውት ነበር።

111 የጌታ እራት ሁል ጊዜ በተሳሳተ መንገድ ተረድተውት ቆይተዋል። አሁን፣ ስለዚህ ጉዳይ ለሰዓታት መቀጠል እችል ነበር፣ ቢሆንም የጌታ እራት እና እግርን-መተታጠብ አለብን። አሁን ከጥቂት የሐይማኖት ተቋማት በስተቀር፡ እግር-መተታጠብን ትተውታል። ብዙ ጴንጤቆስጤዎች ሙሉ በሙሉ ረስተውታል። አያችሁ? አሁንም ልክ እንደ ተጻፈው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ይገኛል። አያችሁ?

112 አሁን፡ ሮም "የጌታ እራት" ብላ አትጠራውም። "ቅዳሴ፡ ቅዱስ ቅዳሴ" ብለው ይጠሩታል። ያስቀድሳሉ እንጂ፡ የጌታ እራት አይወስዱም። ቅዳሴ ነው፡ እና አንድ በእርግጠኝነት ቅዳሴ የጌታ እራትን ትርጉም ያሰወግዳል። **ቅዳሴ** ማለት "ተሰፋ ማድረግ" ነው። ቅዳሴን ሲያደርጉ፡ ተሰፋ በማድረግ (በቅዳሴ ይህን በማድረጋቸው) እግዚአብሔር ኃጢአታቸውን ይቅር እንዲላቸው ተሰፋ ያደርጋሉ፡ ምክንያቱም "የክርስቶስን የሰውነቱ ሥጋ፡ ማለት ካህኑ የክርስቶስ ሥጋና ደም እንዲሆን ይለውጠዋል፡" ይህን በማድረጋቸው፡ እግዚአብሔር ኃጢአታቸውን እንደሚያሰወግድላቸው ተሰፋ አድርገው ይወስዱታል። ቅዳሴ ነው።

113 ፕሮቴስታንቶች "የጌታ እራት" ይሉታል። የጌታ እራት ማለት "ምስጋና።" ፕሮቴስታንቶች… ካቶሊኮች ቅዳሴ ያስቀድሳሉ፡ በዚያ ቅዳሴ እግዚ ኤብሔር ከክፉ ስራቸው ይቅር እንዲላቸው ተሰፋ ያደርጋሉ። በፕሮቴስታንቱ ከእግዚአብሔር ጋር ባለው አንድነት ስለተደረገው ነገር ከምስጋና ጋር ይወስዳል፥ ከእርሱ ጋር መነጋገር፡ አስቀድሞ መፈጸሙን ያመለክታል። ካቶሊኮች ይፈጸም ዘንድ ተሰፋ በማድረግ ሲሆን፡ ፕሮቴስታንቶች ተፈጽሞ ማብቃቱ ይናገራል። ካቶሊካዊው ኃጢአቱ ይቅር ተብሎልኝ ይሆን በማለት ይቅበዘበዛል፥ ፕሮቴስታንቶች ይቅርታ እንደተደረገላቸው፣ ነፃ መሆናቸውን ይመሰክራሉ። የጌታ እራት ግን ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገር ነው። የምንወሰዳቸው እነዚህ አንቀጾች፡ ኃጢአታችን ይቅርታ ተደርጎልናል ብለን **ተሰፋ** አድርገን ሳይሆን፡ ይቅርታ በመደረግጉ **ነው**። በእርግጥ… ለአንዱ ተስፋ ነው፣ ለሌላው እምነት ነው። አንደኛው ልክ ስለመሆኑ ተሰፋ ያደርጋል፡ ሌላውኛ በርግጥ ልክ እንደሆነ ያውቃል። አያችሁ? ሌላኛው፡ የት እንዳለ ስለማያውቅ፡ ተሰፋ ያደርጋል፥ ሌላኛው እግዚአብሔር የተናገረውን ስለሚያውቅ፡ በሥርዓት ልክ እንደሆነ ያውቃል። ያ ነው። ልዩነቱ ይሄ ነው። ስለዚህ፡ ተሰፋ የምታደርግ ከሆነ፡ ተጠንቀቅ፥ ባረጋገጥክ ጊዜ ግን፡ ቀጥል። አየህ፣ ያኔ ከእግዚአብሔር

ጋር ህብረት አለህ። ፕሮቴስታንት፣ ይቅርታ ተደርጎልኛል ብሎ ያውቃል፣ ካቶሊካዊው ወደ ቅዳሴ ይሄዳል፡ ይቅር እንደሚለው ተስፋ ያደርጋል። ልክ እንደዚህ ነው፥ አንደኛው ለማኝ ነው፡ ሁሉም ነገር ደህና እንዲሆን ተስፋ የሚያደርግ፡ አያችሁ፥ ሌላው ስለተደረገው ነገር እያመሰገነ የሚለምን ነው። ሁለቱም ለማኞች ናቸው። ነገር ግን አንደኛው እንደሚያገኘው ተስፋ በማድረግ እየለመነ ሲሆን፥ ሌላኛው ለማኝ እንዳገኛት ያውቃል፡ በዚህም ለእርሱ ስለተሰጠው እርሱን ያመሰግንበታል። እና፡ ልዩነቱ ይኸው ነው። የጌታ እራት ይህ ነው። አዎን፡ ወዳጄ። አንደኛው ይቅርታ እንዲደረግለት ተስፋ ያድርጋል፥ ሌላኛው ይቅር መባሉን ያውቃል፡ ለዚህም ምስጋና ያቀርባል።

114 ስለዚህ፡ የጌታ እራት ከእግዚአብሔር መንፈስ ዳግመኛ ለተወለዱ ክርስቲያኖች ነው። **ዳግመኛ መወለድ** ማለት ግን የግድ መንፈስ ቅዱስ ተሞልተሃል ማለት አይደለም። አሁን ልብ በሉ። እና፡ ብዙዎች ግን ይህንን ያስተምራሉ። "በዚህ መልኩ የሚያስተምር ሰው እኔ አላውቅም፡" አለ ሽማግሌው ወንድም አርጋንብራይት በመድረኩ ላይ በነበረው ምሽት እዚህ እንደተናገረው፡ አያችሁ። ነገር ግን፡ አዲስ ልደት የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ አይልም፡ አያችሁ፡ በእኔ እይታ፡ አይመስለኛም። አያችሁ? ዳግም እንደተወለዳችሁ አምናለሁ…

115 ጥምቀት የሚለውን ቃል በኢየሱስ ክርስቶስ ስም የምጠቀምበት ምክንያት ይህ ነው፣ ነገር ግን ለዳግም ልደት አይደለም። አሁን፣ የጴንጤቆስጤ ቤተ ክርስቲያን፣ የተባበሩት የጴንጤቆስጤ ቤተ ክርስቲያን፣ ለዳግም ልደት በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ታጠምቃለች። እኔ ይህን አላምንም። ከፈለጉ ሊያደርጉት ይችላሉ። እኔ ግን ጴጥሮስ በመጀመሪያ፡ "ንስሐ ግቡ፡" እንዳለ አምናለሁ። ውሃ ኃጢአትን አያስተሰርይም። የቸርች ኦፍ ክራይስትም በዚህ መንገድ ትሰብካለች። እኔ ግን ንስሐ፣ አምላካዊ ጸጸት፣ **ንስሐ መግባት** ማለት "አቅጣጫህን መቀየር፣ መመለስ" ማለት ነው፣ መስመር ስተሃል፡ "እንደገና መጀመር" ማለት ነው። መጀመሪያ ይህንን አድርግ! እናም የውሃ ጥምቀትህ በውስጥህ ላለው ነገር ውጫዊ መናዘዝ ብቻ ነው፡ ማለት ክርስቶስን እንደ አዳኝህ ተቀብለሃል ነው።

116 እንደሚመስለኝ፡ ዛሬ ማታ እዚህ ያሉት የቤተክርስትያን ሰዎች ብቻ እንደሆኑ እገምታለሁ፣ በብዛት እዚህ ስለሌለው ማን እንደሚመጣ ወይም እንደማይመጣ ለማወቅ አልችልም። በአንድ ወቅት፡ እዚህ ገንዳ ውስጥ አንድ ሽማግሌ በማጥመቄ ትችት ደርሶብኛል። ወደ እርሱ ሄድኩኝ፡ መልካም ሽማግሌ ሰው ነው። መላ ቤተሰቡን ወደ ክርስቶስ የመምራት እድል አግኝቻለሁ፣ ሁሉም ክርስቲያኖች ናቸው። እኚህ ሽማግሌ ጥሩ አዛውንት ነበርና፡ ወደድኩት፡ እና ወደ እሱ ሄጄ፡ "ባባ፡ ለምን ክርስቲያን አትሆንም" አልኩት? እሱ ይወደኛል።

117 እርሱም፣ "ወንድም ብራንሃም፣ ጥሩ ሰው ስሆን ክርስቲያን እሆናለሁ" አለኝ።

118 እኔም፣ "ባባ፡ ምን ማድረግ እንዳለብህ ልንገርህ። ጥሩ ሰው መሆን የምትችልበትን ቦታ ፈልጋትና፣ ከዛ በኋላ ቦታውን ንገረኝ፣ እኔም፡ ወደዚያ መሄድ እፈልጋለሁ" አልኩት። "ክርስቶስ ጥሩ ሰዎችን ሊያድን ፈጽሞ

አልመጣም። ክፉ ሰዎችን ለማዳን መጣ እንጂ፡" አልኩት። ጥሩ እንደሆንክ ስታስብ፡ እርሱ ሊያድንህ አይመጣም። ክፉ የሚላቸውን ለማዳን መጣ። አየህ? ክርስቶስ ኃጢአተኞችን ለማዳን ሞተ። አየህ? "ባባ፡ ሚዛኑ ይህ ነው፡" አልኩት።

"ይኸውልህ፡ እኔ'ኮ ሲጋራ አጨሳለሁ፡" አለኝ።

"ስለ እነዚህ ምንም ነገር አልናገርህም፡" አልኩት።

እሱም "ወንድም ብራንሃም፣ ይሄን ለማቆም ሞከርኩ፡" አለኝ።

እኔም "እሺ፣ ስለ ሲጋራ እናወራም፡" አልኩት።

እርሱም "እሺ፡ ስችል... " አለኝ፡

119 እኔም "ስለ—ስለእሱ ምንም አትናገር፣ ዝም ብለህ ተወው። አንድ ጥያቄ ልጠይቅህ እፈልጋለሁ፡" አልኩት።

እሱም፡ "እሺ፡ ምንድን ነው" አለኝ?

እኔም፡ "እምላክ እንዳለ ታምናለህ" አልኩት?

120 "በእርግጥ፡ አምናለሁ፡" አለኝ። እሱም "ወንድም ብራንሃም፡ አንተ እንደምታምነው አምናለሁ ብዬ፡ አስባለሁ፡" አለኝ።

121 እኔም፣ "ይህ አምላክ የራሱን መስመር አልፎ ሰውን ያድን ዘንድ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ማንነት በእኛ እንዳደረ ታምናለህን? "

እርሱም፣ "አዎ፣ አምናለሁ" አለኝ።

"እንደ አንተ እና እንደ እኔ ያሉ ኃጢአተኞችን ለማዳን እንደሞተስ? " አየህ?

"አዎን፡ አምናለሁ።"

122 እኔም፡ "እንግዲህ፣ ነገሩ እንዲህ ነው። ሁላችንም በአንድ ትልቅ ሕንፃ ውስጥ ነን፡ እስር ውስጥ ነን፡ እና እዚህ ጥግ ላይ ቆሜ '**ይህ** ከእስር ቤት ለመውጣት ይረዳኛል' ማለት አልችልም፡ ወይም እዚያ ጥግ ላይ ቆሜ '**ያኛው** ከእስር ያሰወጣኛል አልልም፡' ሁላችንም አንድ አይነት ችግር ውስጥ ነን። ወደዚህ ዓለም የተወለደ ሰው ሁሉ በኃጢአት ተወልዷል፣ በዓመፅ ተጸንሷል፣ ወደ ዓለም የመጣው ውሸት እየተናገረ ነው። ከመነሻው፡ ምናምንቴ ነው።"

123 በቀደም አንድ ሰው፡ ጥያቄ ጠየቀ፡ "ወንድም ብራንሃም፣ በ... በአዳምና በሔዋን እንዲሁም በልጆቻቸው መካከል፡ ልዩነት ይኖር ይሆን፡ ዛሬ እራቁት ቢሆኑ ኖሮ፣ እንዲሁ ቢራመዱ... ሰውነታቸው አንድ ዓይነት ይ—ይሆን ነበርን? "

124 እኔም፡ "በጭራሽ፡ ወዳጄ" አልኩኝ። ወንድም ፍሬድ እና እኔ፡ ከሌሎቹ ጋር አብረን፡ ሽኮኮ አድነን ወደ ቤት እየተመለስን ነበርን። "በጭራሽ፡ ተመሳሳይ አይሆንም ነበር፡" አልኩት።

125 "ሔዋን እንደ ሴት ልጆቿ ሴት አትሆንም ነበር፡ እና አዳምም እንደ ወንድ ልጆቹ ወንድ አይሆንም ነበር ማለትህ ነው፡" አለኝ?

"በብዙ መልኩ፡ በአካላዊ መልኩ ግን አይደለም፡" አልኩት።

እንዲህም አለ፡ "ልዩነቱ ምን ይሆን ነበር? "

126 "እምብርት አይኖራቸውም ነበር። አዎን። ከምንም ጋር የተጣበቀ ነገር አልነበራቸውም። የተፈጠሩ ናቸው።" አልኩት።

127 በዚህ ዓለም ውስጥ የተወለዱትን ነገሮች ሁሉ እስከተሸከመ ድረስ፣ ከጅምሩ፡ ምናምንቴ መሆኑን ያሳያል። አዎን። አልኩትም፡ "በትክክል፡ ልዩነት ይኖራል። እምብርት አይኖራቸውም ነበር። ወደዚህ ለመምጣት፡ ከማንም ሴት ጋር አልተጣበቁም ነበር።" አየህ፡ እግዚአብሔር ፈጠራቸው።

128 አሁን፡ እንዲህ አልኩት። "የሆነ ነገር ማለት እፈልጋለሁ። ሰው ሁሉ በዚህ እስር ቤት ይኖራል፡ ቅዱስ ማን ነው? በወሲብ ያልተወለደ ማን ነው? አንዱ ምንም ቢሆን፡ ሌላውን የሚረዳው ማን ነው? ሁላችንም በዚሁ ተመሳሳይ እስር ቤት ውስጥ ነን። እግዚአብሔር ግን ራሱን ከፍጡራኑ አድርጎ ከጾታዊ ግንኙነት ባሻገር፣ ራሱን በፈጠረው ቅዱስ ደም፣ በዚያ በደሙም እኛን አዳነን።" "ይሄን ታምናለህ፡ ባባ፡" በማለት ጠየቅኩት?

"ይሄን አምናለሁ፡" አለ።

129 እኔም፡ "ክርስቶስ የሞተው እንደ አንተ ላሉ ክፉ ሰዎች ነው። አሁን፡ እዚያ ለመድረስ አንድ መንገድ ብቻ አለ። ሌላ ምንም ማድረግ አትችልም። እሱ ይህንን ለአንተ አቅርቦልሃል። የሚገባህ አልነበርክም። ያንን ለማግኘት ምንም ማድረግ አይቻልህም። እሱ እንዲሁ ሰጥቶሃል። ከገሃነም ለመራቅ፡ ያደረገልህን መቀበል ትፈልጋለህን? "

130 እርሱም፡ "እቀበላለሁ" አለ። "ምነው እነዚህን ሲጋራዎች ማጥፋት በቻልኩኝ፡" አለ።

131 እንዲህ አልኩት፡ "ሲጋራዎቹ በራሳቸው ይጠፋሉ። ብቻ አንተ... እኔ እሱን አልጠይቅህም። ወግ አጥባቂም አይደለሁም። በጸጋ አምናለሁ። 'አብ የሰጠኝ ሁሉ ወደ እኔ ይመጣሉ።'" እንዲህ አልኩት፡ "ይሄን በሙሉ ልብህ ብታምን!"

እሱም "በሙሉ ልቤ፡ አምናለሁ፡" አለኝ።

132 "ታዲያ በዚህ መሰፈርት፡ ማለትም አንተ ለእርሱ ብቁ አለመሆንህ፣ እርሱ ብቻ የበቃ እንደሆነበት በዚህ መሰፈርት ትቀበለዋለህን? ራስህን አትመልከት፥ ለራስህ ምንም ማድረግ ስለማትችል፡ እሱን ተመልከት። አንድ ነገር ያደረገልህን እርሱን ተመልከት። ምን ይመስልሃል? "

"ኦህ፡" "እርሱ ብቁ ነው፡" አለ።

"በቃ፡ እንግዲያውስ እሱ የሰጠህን ተቀበል፡" አልኩት።

"ተቀብያለሁ፡" አለኝ።

133 እኔም በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አጠመቅሁት። እና ከዚህ ወጥቶ ሲጋራ ለኮሰ።

134 ከጥቂት ሳምንታት በፊት ወደ መኖሪያ ቦታው ወርጄ ነበር። አንድ ቀን ሌሊት ራእይ አይቼ፤ የማይረግፍ ዛፍ ተቆርጦ ተገልብጦ አየሁ። በላዩ ላይ የተቸነከሩ ስሌዳዎችም አየሁ። ከመጨረሻው ስሌዳ ቀጥሎ አንድ አስደናቂ ስሌዳ ነበር። እና ከዚያ ስሌዳ በታች፣ ልክ ወደ መጨረሻው አካባቢ፣ **እንደዚህ** ወደ ማለቂያው፣ ዛፉ ላይ እዚያው ተሰብሮ ነበር። ድምፅም እንዲህ አለ፡ "አንተ መሆን ነበረበት፡" ወይም፣ "አንተ በሆንክ ነበር።" ከዚያ ባባ ኮክስ ወድቆ፡

ጀርባውን **እዚህ** ጋር ተጎዳ። በማግሰቱ ጠዋት አልጋ ላይ ሳለ ሲጋራውን ወደ እሱ አመጡለትና፡ ለካ ሱሱ ለቆታል። ከሳምንታት በፊት! አንድም አልቀመሰም፡ እንደውም ፍላጎት የለውም። እያችሁ? ቀደም ሲል አይቼው ነበር፡ ከሳምንታት በቂት፡ በሲጋራ ምክንያት፡ እጆቹ ሁሉ ቡኒ ሆነው የነበረ ሲሆን፡ አሁን አጠገቡ ቢጠጋ መቋቋም አይችልም። ቀዳሚ ነገር አስቀድሙ! ጥሩ ለመምሰል አትሞክሩ፡ ሲጀመር፡ ክፉዎች ናችሁ፡ ምንም ማድረግ አትችሉም። አንድ የመለያያ መስመር አለች፡ የሰው ልጆች በሙሉ በዚያ በኩል ናቸው።

135 እንግዲህ፣ እኔ ወደዚህ ዓለም ሰወለድ፣ በአባቴ እና በእናቴ መካከል በተደረገ፡ በተቀደሰ የጋብቻ ቃል ኪዳን ነበር፤ በማህፀንዋ ውስጥ እንቁላል ነበራት፣ በአባቴ በእጢዎቹ ውስጥ የደም ሕዋስ ነበረው። ህይወቴ የመጣው ከዚያ የደም ሴል ነው (ከእናቴ እንቁላል አይደለም)፡ ከአባቴ የደም ሴል ነው። ይህ የደም ሴል ከእንቁላሉ ጋር ለመገናኘት ቦታው ላይ ሲሄድ፣ ይህን ተከትሎ፡ እግዚአብሔር ተፈጥሮን ሰውነቴን እንድትሰጠኝ አዘዛት። ያኔ ነው በሰው ዘር ዘንድ መወለድ የቻልኩት፡ እንደ ሰው ልጆች ብልህ ሰው ለ—ለመሆን እድል አገኘሁ፣ መኪና መንዳት፡ ወይም የሰው ልጆች እንደሚያደርጉት ነገሮችን ለማድረግ ቻልኩ፡ መራመድ፣ ማውራት፣ መኪና መንዳት፡ እና የመሳሰሉት። ከሰው ቤተሰብ ውስጥ ሰለ ተወለድኩ፡ ይህ ለእኔ ተሰጠኝ፡ ሰው የምሆንበት ሰዋዊ ብልሃት ለእኔ ተሰጠኝ።

136 አሁን፣ ከእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ ሰወለድ፣ በደም መጣሁ፣ ደሙ ሕይወት ሰጠኝ። በክርስቶስ ሕያው ከሆንኩ በኋላ፡ የእግዚአብሔር ልጅ እሆን ዘንድ፡ በመንፈስ ቅዱስ እና በኃይል አጠመቀኝ። አሁን፣ ልክ እንደ ሰው መራመድ፣ መናገር እንደምችል፡ መኪናዬን እንደ ሰው መንዳት እንደምችል፣ መንፈስ ቅዱስን በተቀበልኩ ጊዜ፣ አጋንንትን የማሰወጣት፣ አዲስ ቋንቋ ለመናገር፣ ወንጌልን ለመሰበክ፣ በሽተኛን ለመፈወስ ኃይልን ተቀብያለሁ። ተጠምቄያለሁ! አልተወለድኩም፥ ግን ተጠመቅኩ!

በላይኛው ክፍል ውስጥ ተሰብስበው፡
ሁሉም በሰሙ ሲጸልዩ፡
በመንፈስ ቅዱስ ተጠመቁ፡
ለአገልግሎትም ኃይል ተቀበሉ።

137 አሜን። የዘላለምን ሕይወት ለመቀበል አምናችኋል፡ በገዛ እምነታችሁም ዳግም ተወልዳችኋል። ኢየሱስ፡ በቅዱስ ዮሐንስ 5፡24 ላይ፡ "ቃሌን የሚሰማ የላከኝንም የሚያምን፡ የዘላለም ሕይወት አለው።" ሲል የዘላለም ሕይወት አለው እንጂ፡ መንፈስ ቅዱስ አይደለም። የተወለደው ወደ እግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ ነው። ከዚያም ወደ መንፈስ ቅዱስ ይጠመቃል፡ ከእምነትን የመረዳት ኃይል ጋር፡ ወንጌልን አምኖ በተግባር ላይ እያዋለ እንደሚገባው ይሠራል። ኣሜን። ያን ጊዜ እንደ እግዚአብሔር ልጅ ይመላለሳል። ያን ጊዜ አጋንንትን ማሰወጣት ይችላል። ኢየሱስም እናዳለው፡ "እነዚህ ምልክቶች ይከተሏቸዋል!" እያችሁ? "በሰሜ አጋንንትን ያወጣሉ፡ በአዲስ ቋንቋ ይናገራሉ፡ እባቦችን ይይዛሉ፡ የሚገድልም ይጠጣሉ።" እያችሁ፣ እነዚህን ለማድረግ ከመንፈስ ቅዱስ ኃይልን ይቀበላሉ።

138 አሁን፡ እሱ ሲሄድ፡ እንዲህ አላቸው፡ “እኔ መሄዴ ይጠቅማችኋል። ምክንያቱም፡ እኔ ካልሄድኩ፡ መንፈስ ቅዱስ አይመጣምና።” አያችሁ? ሲመጣም፡ ስለ ኃጢአት ዓለምን ይወቅሳል፡ እርሱ ጽድቅን ያስተምራል፡ እናም የሚመጡትን ነገሮች ያሳያችኋል (እነዚህ ራእዮች ናቸው)። “እኔ ያስተማርኋችሁ ወስዶ፡ ይገልጥላችኋል።” የመጣባቸው ቃላቶች... የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀትን ሳይቀበል ቃሉን ሊረዳ የሚችል ማንም የለም። ሰው የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ተቀብያለሁ እያለ፡ የቃሉን እውነት ሲከራከር፡ አንድ ችግር አለ።

139 ጳውሎስ የአዲስ ኪዳን ተቃዋሚ ነበር። አይደለም፡ አዲስ ኪዳን ገና አልተፃፈም ነበርና። ጳውሎስ፡ ሳኦል የክርስትና ተቃዋሚ ነበር። መንፈስ ቅዱስንም በተቀበለ ጊዜ፡ ወደ እስያ ሄደ በዚያም ሦስት ዓመት መጽሐፍ ቅዱስን አጠና፡ ምክንያቱም ታላቅ አስተማሪ በነበረው፡ በገማልያል እግር ስር የተማረ ስለነበረ። ከዚያም ከአሥራ አራት ዓመት በኋላ፡ ጴጥሮስን ሊገናኘው፡ ወደ ኢየሩሳሌም ወጣ። ወንጌላቸውም ቃል በቃል አንድ ሆኖ አገኘው። በበዓለ ሃምሳ ቀን ጴጥሮስ እንዲሰብክና ለሕዝቡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እንዲጠመቁ የነገራቸው አምላክ፣ ያ መንፈስ ቅዱስም ለጳውሎስ ገልጾለታል፣ በአንድ ወቅት በዮሐንስ ተጠምቀው የነበሩትን በሐዋርያት ሥራ 19 ላይም ተናገራቸው፡ “በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ ዳግም ልትጠመቁ ይገባል፡” አላቸው። አያችሁ?

140 አያችሁ፣ መንፈስ ቅዱስ ሁሉ ጊዜ ከቅዱሳት መጻሕፍት ጋር በጥብቅ ይስማማል። በእሱ ላይ ያላችሁ እምነት እያንዳንዱን ምስጢር ይከፍትላችኋል። ኣሜን። መጽሐፍ ቅዱስ፡ በ1ኛ ዮሐንስ 5፡7 እንዲህ ይላል፡ “በሰማይ የሚመሰክሩት፡ ሦስት ናቸው፣ አብ፣ ቃል (እርሱም ክርስቶስ)፡ እና መንፈስ ቅዱስ። እነዚህ ሦስቱ አንድ ናቸው።” “በምድር ላይ የሚመሰክሩት ሦስቱ ደግሞ፡ ውኃው፣ ደሙ፣ መንፈስ ናቸው። እነዚህ ሦስቱ አንድ አይደሉም፡ ነገር ግን በአንድ ይስማማሉ።” ማምለት፡ ወልድ ሳይኖራችሁ አብ ሊኖራችሁ አይችልም፣ መንፈስ ቅዱስ ከሌለ ወልድ አይኖራችሁም፥ አንድ ናቸው። ሳትቀደሱ ግን ልትጸድቁ ትችላላችሁ፡ መንፈስ ቅዱስም ሳይኖራችሁም ልትቀደሱ ትችላላችሁ። መቀደስ በደም ነው፡ ሕይወትም የሚመጣው በደም ነው። አያችሁ? መንፈስ ቅዱስም የእግዚአብሔር ኃይል ነው፡ አያችሁ፡ ለቤተክርስቲያን የተሰጠው ኃይል ነው።

141 “ትቀበላላችሁ” (ምን?) “ኃይል፡” ሐዋ 1፡8፣ “መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ ይመጣል። ኃይልን ትቀበላላችሁ!” (“ዳግመኛ ትወለዳላችሁ” አይደለም።) “መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ። በኢየሩሳሌምም፡ በይሁዳም፡ በሰማርያ፡ እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ።” አያችሁ? መንፈስ ቅዱስን ከተቀበላችሁ በኋላ ኃይልን ትቀበላላችሁ። መጀመሪያ ግን መንፈስ ቅዱስን መቀበል አለብህ፣ ያም እንድንገልጥ እና እንድንሰራ፡ አያችሁ፡ የእግዚአብሔር ኃይል ነው። እናንተ ናችሁ—እናንተ ናችሁ... የሰው ልጅ፡ እንዲናገርና እንዲራመድ እና ሰው የሚያደርገውን ነገር እንዲያደርግ እንደተማረው ሁሉ፥ በመንፈስ ቅዱስም ስትጠመቁ፡ እንደ እግዚአብሔር ወንድና ሴቶች ልጆች እንድትሆኑ ኃይል ተሰጥቷችኋል። ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተው ስለማያውቁ፡ ዛሬም

እንደወደዱት ቢያደርጉ እና ቢሰሩ ምንም አያስደንቅም። ቢሞሉ ኖሮ፡ በሌላ መንገድ ይሰሩ ነበር። ተሞልተናል ይላሉ፡ ኢየሱስ ግን፡ “ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ” ብሏል። ታዲያ እንዴት ትችሉታላችሁ፡ አያችሁ፡ ሁሉም ነገር የተገለባበጠ ነው። አያችሁ? ግን ወደ እውነታው ተመለሱ!

142 አሁን፣ ኑሮአችሁ ትክክል ከሆናችሁ እና ክርስቲያን ነኝ ካላችሁ፣ ዛሬ ማታ ወደ ጌታ ማዕድ እንጋብዛችኋለን። ዛሬ፡ የጌታ እራት፡ በመላ አገሪቱ እየተደረገ ይገኛል፣ አንዳንዶቹ በአንድ መንገድ አንዳንዶቹ በሌላ መንገድ እንደሆነ አያጠራጥርም። ብትወስዱ ግን የተሻለ መንገድ የሚሆነው ቅዱስ ቃልን በመከተል ነው፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዳደረጉት በማድረግ ነው። ይህ በቂ ነው ብዬ አስባለሁ።

143 ወንድም ኔቪል፡ መጽሐፍ ቅዱስህን ይዘሃል? ወንድም ኔቪል አሁን መጽሐፍ ቅዱስ ያነብልናል።

[ወንድም ኔቪል እንዲህ አለ፡ “በአንደኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 11፣ ከቁጥር 23 ጀምሮ፡”—አርታዒ።]

**[ለእናንተ ደግሞ አሳልፌ የሰጠሁትን ከጌታ ተቀብያለሁና፡ ጌታ ኢየሱስ አልፎ በተሰጠበት በዚያች ሌሊት እንጀራ አንሥቶአልና፡]**

**[አመሰገነም፡ ቈርሶም፡ እንካችሁ፡ ብሉ፡ አላቸው፥ ይህ ስለ እናንተ፡ የተቆረሰ ሥጋዬ ነው፤ ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት።]**

**[እንዲሁም ደግሞ እራት ከበላ በኋላ ጽዋውን አንሥቶ፡ ከቀመሰ በኋላ፡ ይህ ጽዋ በደሜ የሚሆን አዲስ ኪዳን ነው፡ አላቸው፥ በጠጣችሁ ጊዜ ሁሉ፡ ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት፡ አላቸው።]**

**[ይህን እንጀራ በበላችሁ ጊዜ፡ ይህንም ጽዋ በጠጣችሁ ጊዜ ሁሉ፡ ጌታ እስኪመጣ ድረስ ሞቱን ትናገራላችሁና።]**

**[ስለዚህ ሳይገባው፡ ይህን እንጀራ የሚበላ፡ ወይም የጌታን ጽዋ የሚጠጣ ሁሉ፥ በጌታ ሥጋና ደም በደለኛ ይሆናል።]**

**[ነገር ግን ሰው ራሱን ይፈትን፥ ከዚያም ከዚያ እንጀራ ይብላ፡ ከጽዋውም ይጠጣ።]**

**[ሳይገባው የሚበላና የሚጠጣ፡ የጌታን ሥጋ ስለማይለይ፡ ለራሱ ፍርድ ይበላልና ይጠጣልምና።]**

**[ስለዚህ በእናንተ ዘንድ የደከሙና የታመሙ ብዙዎች አሉ፡ ብዙዎችም አንቀላፍተዋል።]**

**[ራሳችንን ብንመረምር፡ ባልተፈረደብንም ነበርና።]**

**[ነገር ግን በተፈረደብን ጊዜ፡ ከዓለም ጋር እንዳንኮነን፡ በጌታ እንገሠጻለን።]**

[“ጌታ የቃሉን ንባብ ይባርክ።”]

144 ሁል ጊዜ እንደዚህ ያለ ቅዱስ ነገር ነው፡ እንደዚህ ያለ የተቀደሰ ነገር ነው አሁን በጽሞና ጸሎት፡ አንገታችንን ዝቅ ማለት ያለብን ይመስለኛል። እናንተ ጸልዩልኝ፡ እኔም እጸልይላችኋለሁ። እግዚአብሔር ለእኛ ለማይገባቸውን ፍጥረታት እንዲምረን፡ እርስ በርሳችን እንጸልይ ይህም የጌታችንን ሞት በማሰብ ከዚህ ታላቅ ቅዱስ ቁርባን ለመካፈል ነው።

145 [ወንድም ብራንሃም በጽሞና ለመጸለይ አቆመ። በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ—አርታዒ።] አቤቱ ለአንተ ለአባታችን፣ በወርቅ መሠዊያህ ላይ፣ ከመሥዋዕታችን ጋር፣ ይህንን የኑዛዜ ጸሎት፣ ከጌታ ኢየሱስ ጋር እናቀርባለን። በስሙ እንጠይቃለን። ኣሜን።

146 አሁን ሽማግሌዎቹ ቦታቸውን እንደሚይዙ አምናለሁ፣ እናም እነሱ... ከቤተ ክርስቲያን፣ ህዝቡ ስለ ጌታ እራት ሲያልፍ፡ መደዳ በመደዳ፡ ያሳልፏቸዋል። ሁልጊዜ ይሄን መዝሙር አስባለሁ፥

የሞትከው በግ ሆይ፡ ክቡር ደምህ
ኃይሉን በፍጹም አይደክምም፡
የተዋጁ የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን
ኃጢአት ላይሰሩ፡ እስኪድኑ ድረስ።

ራሶቻችንን ዝቅ እናድርግ።

147 ቸር እና ቅዱስ አባት ሆይ፣ ሁሉን ቻይ የሆንከው፡ ጀሆቫ፣ በምንጠብቅ ጊዜ በረከቶችህን በሕዝብህ ላይ ላክ። ኃጢአታችንን ይቅር በለን። እና አሁን ይህን ቅዱስ ቁርባን፡ ይህን ወይንን፡ የበቀለውን ይህ ወይን፣ እነሆ እነዚህ የአገልጋዮች እጅ በአንድ ላይ ጨምቀውታል። እነሆ አሁን ወደ አንተ ስለምናመጣው ነገር ወይን ሆኖ ተዘጋጀ፡ ይህም የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ደም ለእኛ ይወክል ዘንድ ነው። አባት ሆይ፡ ወይኑን ለዚያ ዓላማ ትቀድሰው ዘንድ፡ እጸልያለሁ። በደላችንን ሁሉ ይቅር በል። እናም ይህን ወይን ወደ ሰውነታቸው የሚቀበል ሁሉ ጤና፣ ጥንካሬ፣ እና መዳን፣ ከአንተ ዘንድ ይሁን። ይሁን፡ ጌታ ሆይ። በኢየሱስ ስም እንጠይቃለን። ኣሜን።

148 መጽሐፍ ቅዱስ ሲናገር እንጀራ ቆርሶ በባረከ ጊዜ እንዲህ ይላል፡ "እንካችሁ ብሉ፡ ይህ ለእናንተ የተቆረሰ ስጋዬ ነው። ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉ፡" ይላል። እና እነዚህን ቁርሰራሽ፡ የዳቦ ህብስቶች ሰንወሰድ፡ በክርስቲያኖች እጅ፡ ያለ ምንም እርሾ የተዘጋጀ ነው፡ የተሰራው—የክርስቶስን አካል ስለሚወክል ነው። ይሄን—ተረድተናል ይህም በክርስቶስ የመጨረሻው እራት፡ በመጨረሻው እራት ላይ፡ የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት ቀን፡ ወይም የቤተክርስቲያን ቀን እንደነበረ ይሄን እናውቃለን። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥም፣ እነዚህን ነገሮች ለሕዝቡ ያገለገሉት ደቀ መዛሙርት ናቸው። ዛሬም፡ የሰለጠነው-ዘመን ደቀ መዛሙርት፡ እዚህ ያሉት የቤተ ክርስቲያን ወንድሞቻችን፣ የዚህ ጥሪ ደቀ መዛሙርት፣ ሕዝቡን ያገለግላሉ። እነዚህንም ቁርሰራሾች ወስደው ለሕዝቡ ያከፋፍላሉ።

149 እና አሁን ይህን ህብስት ስትቀበሉ፡ የበጉ ተምሳሌት እንደሆነ፡ አስታውሱ። ከብዙ አመታት በፊት የእስራኤል በግ በእሳት ሲጠበስ፡ እና በመራራ ቅጠል ሲበሉት፡ ህዝቡ ብርታት አገኙ፥ ጫማቸው በፍጹም አላለቀም፡ ልብሳቸውም

በፍጹም አላረጀም፡ የተሰፋይቱ ምድር እስኪደርሱ ድረስ በጉዞአቸው ሁሉ እንዲሁ ነበር። እግዚአብሔር ወደ ሰጠን የተሰፋይቱ ምድር እስክንደርስ ድረስ በጤና፣ በደስታ፣ በማገልገል ያቆይልን።

እንጸልይ።

150 ቸር የሰማይ አባት፣ ዛሬ ምሽት ስለዚያ ቅዱስ፣ ስለተቀደሰው የጌታችን አካል ስናገር፣ በእርሱም የመለኮት ሙላት ያደረበት፣ ያ አካል በደም መለወሱን እ—እና መሰበሩን ሳሰበው፡ እንዲሁም ደሙ ሲንጠባጠብ አልቆ፡ ጀርባውና የጎድን አጥንቱ እስኪታይ ድረስ፣ ግርፋቱ ጀርባው ላይ እና ታች፣ ይህ የተተለተለ የተመታ ህብስት፡ ይህን የሚወክለው ሳሰበው፡ በልባችን ውስጥ እንደገና ይመጣል፡ ጌታ ሆይ፡ ዛሬ ማታ ልባችንን፡ በመሠዊያህ ስር እናኖራለን። አምላክ ሆይ፡ ይቅር በለን ። ይህም የተቆረሰ ህብስት፡ ወደ እነዚህ ወደ አፋቸው ሲገባ፡ ባርያዎችህ፡ እንዲሁም እነሱ የተቀጠቀጠውና የቆሰለው ክቡር ሥጋህ መሆኑን፡ በመገረፉም እኛ እንደተፈወስን ይወቁ። ይሁንልን፡ ጌታ ሆይ። ይህን የዳቦ ህብስት ለታሰበበት ዓላማ እንዲሆን ቀድሰው። በኢየሱስ ስም እንጠይቃለን። ኣሜን።

አንድ ደቂቃ ብቻ ያዙት።

151 ሌሎችን የማያካትት የጌታ እራት አይደለም። እያንዳንዱ ክርስቲያን አማኝ ከእኛ ጋር ይህን ህብረት ለማድረግ፡ ወደ ጌታ ማዕድ መምጣት ይችላል... ? ...

62-1007 የበሩ መክፈቻ
ብራንሃም ተበርናክል
ጀፈርሰንቪል, ኢንዲያና ዩ.ኤስ.ኤ

AMHARIC

©2025 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

VOICE OF GOD RECORDINGS
P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.
www.branham.org

## የቅጂ መብት ማሳሰብያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው®።

ለተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ቢፈልጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡

VOICE OF GOD RECORDINGS

P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.

www.branham.org